# የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ

## ትምህርት አምስት

# ቤተ ክርስቲያን

## ተርጓሚ፦ እሸቴ በለጠ

## THE APOSTLES’ CREED

## Lesson Five

## The Church

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

# ማውጫ


1. **መግቢያ**
2. **ስምምነት/ፍቃድ**

   ብሉይ ኪዳን

   ኢየሱስ

   አንድምታዎች

      ዓላማ

      አማኞችና የማያምኑ

      ግዴታዎች

3. **ቅዱስ**

   ትርጓሜ

   ህዝብ

      የምትታየዋ ቤተክርስቲያን

      የማትታየዋ ቤተክርስቲያን

4. **ካቶሊክ**

   ትርጓሜ

   የምትታየዋ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን

   የማትታየዋ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን

      አንድ አዳኝ

      አንድ ሃይማኖት

5. **አንድነት**

   የምትታየዋ ቤተክርስቲያን

      ጸጋን የማግኛ መንገድ

      የጸጋ ስጦታዎች

      ንብረት/ቁሳቁስ

   የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን

      ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን

      ከአማኞች ጋር አንድ መሆን

6. **ማጠቃለያ**

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

# ፤. መግቢያ

በዘመነኛው ዓለም፣ አብዛኛዎቹ ሰዎች “ቤተክርስቲያን” የሚለውን ቃል ሲሰሙ የሚያስቡት አማኞች እግዚአብሔርን ለማምለክ ስለሚሰበሰቡበት ሕንፃ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ሕንፃዎች ግዙፍና የተዋቡ፣ በተዋቡ የስነ ጥበብ ሥራዎች የተንቆጠቆጡ ካቴድራሎች ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ትናንሽና መጠነኛ መቀመጫዎች ያሉዋቸው ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከጊዜ በኋላ የተለወጡ የዕቃ ግምጃቤቶች ወይም መጋዘኖች ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ መኖሪያ ቤቶች፣ ደሳሳ ጎጆዎች፣ የጭቃ ቤቶች፣ ምናልባትም አማኞች ከአደጋ የሚሸሸጉባቸው ዋሻዎች ይሆናሉ፡፡ በሐዋርያት የሃይማት መግለጫ ግን፣ ልክ በመጽሐፍ ቅዱስ እንዳለው ሁሉ፣ “ቤተክርስቲያን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከሁሉ አስቀድሞ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ የሚያምኑትን ቅዱስ የእግዚአብሔር ህዝብ አንድነትን ነው፡፡

ይህ ከሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ተከታታይ ትምህርቶቻችን አምስተኛው ትምህርት ነው፡፡ “ቤተክርስቲያን” የሚል ርዕስም ሰጥተነዋል፡፡ በዚህ ትምህርት፣ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ ስለዚህ የተቀደሰ ተቋም የተፃ ፉትን አንቀፆች እንመለከታለን፡፡

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ስለቤተክርስቲያን በግልፅ የሚናገረው በነዚህ ቃላት ነው፡

*በአንዲት የሐዋርያት ቤተክርስቲያን፣*

*በቅዱሳን አንድነት፣*

*... አምናለሁ፡፡*

በሃይማኖት መግለጫው ውስጥ የተጠቀሱት እነዚህ መስመሮች ለመንፈስ ቅዱስና ለአገልግሎቱ ከተሰጠው ስፍራ ትልቁን ይዘዋል፡፡ የዚህም ምክንያቱ መንፈስ ቅዱስ በዕለት ከዕለት የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ ውስጥ በአብዛኛው የሚሳተፍ የስላሴ አካል ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህም፣ ስለ ቤተክርስቲያን ስለ መንፈስ ቅዱስ በተነጋገርንበት ትምህርት ውስጥ ልንነጋገር እንችል ነበር፡፡ ግን ለክርስትና መሠረታዊ ስለሆነና እንደ ክርስቶስ ተከታዮች ሕይወትን እናጣጥም ዘንድ በቤተክርስቲያን ላይ ራሱን የቻለ ሙሉ ትምህርት እንዲኖረን ፈለግን፡፡

ቀደም ባለው ትምህርት እንደገለፅነው፣ በቤተክርስቲያን ላይ ስላለን የእምነት አቋም መግለጡ ለአብዛኛው የፕሮቴስታንት አማኞች ግር የሚያሰኝ ነው፣ ምክንያቱም ስለ ቤተክርስቲያን ያለን የእምነት አቋም ከእግዚአብሔር ጋር ካለን እምነት ጋር ተመሳሳይ መልክ ያለው ስለሚመስል ነው፡፡ የሃይማኖት መግለጫው ግን በቤተክርስቲያን እናምናለን ሲል፣ ለድነት በቤተክርስቲያን

እንታመናለን ማለቱ አይደለም፡፡ የሚያድን እምነት በክርስቶስና በክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ በቤተክርስቲያን እናምናለን የምንለው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቤተክርስቲያን የሚያስተምረውን እና ቤተክርስቲያን ለክርስቲያኖች አስፈላጊ መሆኗን ሲነግረን ማመናችንን ለመግለጥ ነው፡፡ በቅዱሳን አንድነት ስለ ማመናችንም የምንናገረው እንዲሁ ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ለድነታችን በሌሎች አማኞች አንታመንም፡፡ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ ወንጌልን እንዲያደርሱ፣ እንዲያገለግሉንና በእምነታችን እንድንጠነክር እንዲያግዙን እግዚአብሔር ሌሎች አማኞችን እንደሚጠቀም የሚያስተምረውን እናምናለን ማለት ነው፡፡

ስለ ቤተክርስቲያን የምንማረው ትምህርት በሃይማኖት መግለጫው ላይ በተንፀባረቁት አራት ማዕከላዊ ትምህርቶች ይከፈላል፡፡ አንደኛ፣ ስለ ቤተክርስቲያን ያለውን መለኮታዊ ፈቃድ/ስምምነት እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ ቤተክርስቲያን ቅዱስ በመሆኗ እውነታ ላይ እንነጋገራለን፡፡ ሦስተኛ፣ በዓለም አቀፋዊነቷ ላይ እንነጋገራለን፡፡ አራተኛ፣ ቤተክርስቲያን አንድነት የመሆኗን ሃሳብ እንመረምራለን፡፡ እነዚህ ክፍሎች በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ የተጠቀሰችው ቤተክርስቲያን ማንነትና ተፈጥሮ ምን መልክ እንዳለው እንድንገነዘብ ያደርጉናል፡፡ በቤተክርስቲያን መለኮታዊ ስምምነት/ፈቃድ እንጀምር፡፡

# 2. ፈቃድ/ስምምነት

በዘመነኛው ዓለም፣ ቤተክርስቲያን አታስፈልግም ወይንም ያንን የሚመስል አቋም የሚያራምዱ በርካታ ክርስቲያኖች አሉ፡፡ በርካታ እውነተኛ አማኞች ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን የመሰሉ ተቋማት በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ባለ ግንኙነት መሃል ጣልቃ የገቡ የሰው ግኝቶች ናቸው ብለው ያስባሉ፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ግን ከዚህ በጣም የተለየ አመለካከትን ነው የሚያስተምሩት፡፡ ሰፋ ባለው ግንዛቤ፣ ቤተክርስቲያን በምድር ያለች የእግዚአብሔር መንግሥት፣ ለእርሱ የተለየ ሕዝብ ጉባኤ እና ለእርሱ ታማኝ በሆኑት ላይ ለሚያፈስሰው ጸጋ ማዕከል ናት፡፡ እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት አገላለጥ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ለመጀመርና ለመጠበቅ ቤተክርስቲያን እጅግ ወሳኝነት አላት፡፡

ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ፈቃድ ተመሥርታለች ስንል፣ ለዓላማ ፈጥሯታል፣ ሥልጣንንም ሰጥቷታል ማለታችን ነው፡፡ በጥቅል አነጋገር፣ እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን እውቅናን እንደሰጠ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምራሉ፡፡ በዓለም ላይ የእርሱን ተልዕኮ እንድታስፈፅም የተሾመች ተቋም ናት፡፡ በማቴዎስ ምዕራፍ 16 ቁጥር 18 ኢየሱስ ራሱ እንደተናገረው፡

ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም። (ማቴ 16፥18)

ቤተክርስቲያን የወደቀው የሰው ዘር ግኝት አይደለችም፡፡ የቤተክርስቲያን መሥራች ኢየሱስ ራሱ ነው፡፡

ስለዚህ፣ በታሪክ ዘመናት ሁሉ ውስጥ በቤተክርስቲያን የተለያዩ ድካሞችን ብንመለከትም፣ አንዳንድ ጊዜም የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን እስከማይመስሉ ድረስ ከወንጌል እጅግ እርቀው ቢሄዱም፣ ቤተክርስቲያን እርባና የለሽ ወይንም የማትጠቅም ናት ብለን መደምደም የለብንም፡፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ይህንን መለኮታዊ ፈቃድ/ስምምነት በእነዚህ ቀላል ቃላት ነው የሚያረጋግጠው፡፡

*... በቤተክርስቲያን... አምናለሁ፡፡*

እንደምታስታውሱት ቀደም ባሉት ትምህርቶች፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የቀደሙት አብያተ ክርስቲያናት የእምነት አንቀፆች ማጠቃለያ ነው፡፡ እነዚህም የእምነት ህግጋት የቅዱሳት መጻሕፍት ማጠቃለያዎች ናቸው፡፡ እንግዲያው፣ የሃይማኖት መግለጫው በቤተክርስቲያን ስለ ማመን ሲገልፅ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቤተክርስቲያን የሚያስተምረውን ለማረጋገጥ ዓላማ አድርጎ ነው፡፡ ስለ ቤተክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ መሠረታዊ ገፅታ ደግሞ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን የሾመው የእርሱን ዓላማ በምድር እንድትፈፅም ነው የሚለው ነው፡፡

ስለ ቤተክርስቲያን መለኮታዊ ፍቃድ/ስምምነት ስንመለከት፣ በሦስት ዋና ሃሳቦች ላይ እናተኩራለን፡፡ አንደኛ፣ ስለ ቤተክርስቲያን ብሉይ ኪዳናዊ ዳራ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ በእርሱ የምድር አገልግሎት ዘመን ኢየሱስ ቤተክርስቲያንን ለመመሥረት ምን እንዳደረገ እንመለከታለን፡፡ ሦስተኛ፣ የእነዚህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከቶች ጥቂት እንድምታዎች እንዳስሳለን፡፡ በቤተክርስቲያን ብሉይ ኪዳናዊ ዳራ እንጀምር፡፡

# ብሉይ ኪዳን

በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን የተሰኘው ፅንሰ-ሃሳብ መሠረቱ ከብሉይ ኪዳን የተገኘ ነው፡፡

*ብዙዎች የሚያምኑት ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ በሐዋርያት ላይ ባፈሰሰው መንፈስ በበዓለ ሃምሳ ቀን እንደሆነ ነው፡፡ እኔ እንደማስበው ግን ይህ ስለ ቤተክርስቲያን ተፈጥሮ የተሳሳተ አመለካከት ነው፡፡ እኔ እንደማስበው ቤተክርስቲያን በብሉይ ኪዳን የነበሩ የእግዚአብሔር ሕዝብ ቀጣይ ናት፡፡ እግዚአብሔር አብርሃምንና የብሉይ ኪዳንን ሕዝብ ጠርቷል፣ ያም ቤተክርስቲያን፣ የቤተክርስቲያንም ጅማሬ ነው ብለን ማለት እንችላለን፡፡ ቤተክርስቲያን የተጀመረችው እዚያ ነው፡፡ እስከኛም ዘመን ዘልቃለች፣ ጌታም ከሰማያት ተመልሶ እስከሚመጣባት የፍርድ ቀን ድረስ ትዘልቃለች፡፡ [ዶ/ር ሬድ ኬሲስ]*

አዲስ ኪዳን ስለ ቤተክርስቲያን ሲናገር ብዙ ጊዜ የሚጠቀመው ekklesia (ኤክሌሺያ) የተሰኘውን የግሪክ ቃል ነው፡፡ ይህ ቃል የተወሰደው ግን ሰፕቱዋጀንት (ሰብዓ ሊቃናት) ከተሰኘው የብሉይ ኪዳን የግሪክኛ ቅጂ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን፣ ekklesia (ኤክሌሺያ) የተሰኘውና የዕብራይስጥ አቻው በተደጋጋሚ በጥቅም ላይ የሚውሉት በአንድነት የሚሰባሰበውን የእስራኤል ሕዝብ ነው፡፡ ይህንንም በዘዳግም ምዕራፍ 9 ቁጥር 10፣ ምዕራፍ 31 ቁጥር 30፤ መሳፍንት ምዕራፍ 20 ቁጥር 2፤ 1ኛ ነገሥት ምዕራፍ 8 ቁጥር 14፤ መዝሙር 22 ቁጥር 22 እና 25 እና በሌሎችም በርካታ ስፍራዎች እናገኛለን፡፡

በአዲስ ኪዳንም እንኳን፣ ekklesia (ኤክሌሺያ) የሚለው ቃል ቤተክርስቲያንን ለማመልከት ሲገባ፣ ቃሉ አሁንም የብሉይ ኪዳኗን የእስራኤልን መሰባሰብ ለማመልከት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ለምሳሌ፣ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 7 ቁጥር 38፣ እስጢፋኖስ ለገዳዮቹ ባደረገው ንግግር ውስጥ እነዚህን ቃላት እናገኛለን፡

> ይህ ሰው በሲና ተራራ ከተናገረው መልአክና ከአባቶቻችን ጋር በምድረ በዳ በማኅበሩ ውስጥ የነበረው ነው፤ ይሰጠንም ዘንድ ሕይወት ያላቸውን ቃላት ተቀበለ፤ (ሐሥ 7፥38)

በዚህ ስፍራ፣ ማኅበር ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል ekklesia (ኤክሌሺያ) ሲሆን፣ አብዛኛውንም ጊዜ በተለምዶ “ቤተክርስቲያን” ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ማኅበረ እስራኤል የአዲስ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን የብሉይ ኪዳኗ አቻና ቀዳሚ መሆኗን ነው፡፡

በ1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 9 ላይ፣ በብሉይ ኪዳን ለእስራኤል ተሰጥቶ የነበረውን ስም ለቤተክርስቲያን ተጠቅሞበታል፡፡ እስኪ የጻፈውን አድምጡ፡

> እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤ (1ጴጥ 2፥9)

በዚህ ስፍራ፣ ጴጥሮስ ስለ እስራኤል ሕዝብ የተነገሩ በርካታ የብሉይ ኪዳን ምንባቦችን አጣቅሷል፡፡ የእስራኤልንም ልዩ ስም ለአዲስ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን ተጠቅሞበታል፡፡ በዚህም መንገድ፣ በነዚህ ሁለት ወገኖች መካከል እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ተያያዥ ነገሮች መኖራቸውን አመልክቷል፡፡

> *ጴጥሮስ በብሉይ ኪዳን ለእስራኤል ተሰጥተው የነበሩትን ተከታታይ መጠሪያዎች ለቤተክርስቲያንም ከጥቅም ላይ ስላዋለበት ስለ 1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 9*

*"…የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤" ስለሚለው ምንባብ ስናስብ ጴጥሮስ እያስተማረ ያለው በተለያዩ ክፍሎች የሚኖሩና አስቀድመውም አህዛብ የነበሩ አብያተክርስቲያናት ለእስራኤል የአግዚአብሔር ተስፋ ሙላት እንደሆኑ አድርገው ራሳቸውን እንዲቆጥሩና ያም ማንነታቸው መሆኑን እንዲገነዘቡ መሆኑን እንመለከታለን፡፡ [ዶ/ር ዴኒስ ጆንሰን]*

እርግጥ ነው፣ ይህ ማለት ግን የአዲስ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን ከብሉይ ኪዳኗ የእስራኤል ማኅበር ጋር ፍፁም አንድ ናት ማለት አይደለም፡፡ እርስ በርስ የተገናኙ ናቸው፣ ግን የተለያዩም ናቸው፡፡ በሮሜ ምዕራፍ 11 ውስጥ፣ ጳውሎስ ስለብሉይ ኪዳኑ ማኅበረ እስራኤልና ስለአዲስ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን ሲናገር ሁለት ተለዋጭ ዘይቤዎችን ተጠቅሟል፡፡ ስለ በረሃ ወይራና ስለ ወይራ ዛፍ ተናግሯል፡፡

በሮሜ ምዕራፍ 11 ቁጥር 16 ጳውሎስ የተናገረውን አድምጡ፡

> በኵራቱም ቅዱስ ከሆነ ብሆው ደግሞ ቅዱስ ነው፤ ሥሩም ቅዱስ ከሆነ ቅርንጫፎቹ ደግሞ ቅዱሳን ናቸው። (ሮሜ 11፥16)

በመጀመሪያ፣ የብሉይ ኪዳኑ ማኅበር የአዲስ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን የተገኘችበት ወይራ የበኩር ፍሬ መሆኑን ጳውሎስ ይናገራል፡፡

ዘሌዋውያን ምዕራፍ 23 ቁጥር 17 እስራኤል የመከሯን በኩራት የቂጣ መስዋዕት አድርጋ ለጌታ እንድታቀርብ ያዝዛል፡፡ በኩራት የተለየ መከር አይደለም፡፡ የጠቅላላው መከር አካልና የጠቅላላው መከር ማሳያ ነው፡፡ እንግዲያው፣ ጳውሎስ እስራኤልም የአዲስ ኪዳኗ ቤተክርስቲያንም ከአንዱ ወይራ የተገኙ ናቸው ሲል፣ እስራኤልም የአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖችም የአንዱ ተቋም አካል፣ አንድ ዓይነት የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ ተመሳሳይ ቤተክርስቲያን ናቸው ማለቱ ነው፡፡

ሁለተኛ፣ ጳውሎስ እያለ ያለው የብሉይ ኪዳኑ ማኅበር የዛፉ ስር ሲሆን፣ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ደግሞ የዚያው ዛፍ ቅርንጫፍ ናት ነው፡፡ ጳውሎስ ይህንን መግለጫ በበርካታ ጥቅሶች በግልጥ ያብራራዋል፡፡ በዘመናት ሁሉ የነበረችውን ቤተክርስቲያን ከወይራ ዛፍ ጋር ያመሳስላታል፡፡ የብሉይ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን፣ አይሁድን የያዘች ሲሆን፣ ያም የዛፉ ዋና ክፍል፡ ስሮች፣ ግንድና በርካታ ቅርንጫፎችንም ይዟል፡፡ የአህዛብ ክርስቲያኖች ደግሞ በዛፉ ውስጥ የገቡ የበረሃ ወይራ ቅርንጫፎች ናቸው፡፡ የአህዛብ ክርስቲያኖች በአይሁድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተቀላቅለዋል በማለት ጳውሎስ በቀላሉ ያስቀምጠዋል፡፡ ስለዚህ፣ ምንም እንኳን በጳውሎስ ዘመን የነበረችው ቤተክርስቲያን አህዛብንም አይሁድንም የያዘች ብትሆንም፣ ወደ ብሉይ ኪዳን ተመልሰን ታሪክን ወደ ኋላ ስንመረምር ግንዱና ስሩ ግን የዚያው የአንዱ ዛፍ አካላት መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ አዎን፣ ይህ አዲስ ዛፍ በብዙ ገፅታዎቹ የተለየ ነው፡፡ እጅግ የተሻለና እየተገነባ የመጣ

ነው፡፡ ግን የዚያው የአንዱ ዛፍ አካል ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ፣ የብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያን ወደ አዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን በተሻለ መንገድ እየተገነባ ያደገ ነው ማለት ነው፡፡ እጅግ አስፈላጊ በሆነ መንገድ የተለያዩ ናቸው፣ የተለያየ ዕድገት ደረጃንም ይወክላሉ፡፡ ግን የዚያው የአንዱ ዛፍ አካል ናቸው፡፡

በብሉይ ኪዳን ዳራ አንፃር የቤተክርስቲያንን ስምምነት ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን ከብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያን ጋር ተያይዞ እና የተሻለችም ሆና እንድትመሠረት እንዴት እንዳደረገ እንመልከት፡፡

# ኢየሱስ

ኢየሱስ በመጣ ወቅት፣ የምድር አገልግሎቱ በዓለም ላይና በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ አስገራሚ ተጽዕኖ ያሳደረ መሆኑ የማይካድ ነው፡፡ በርካታ የነገረ መለኮት ሊቃውንት ኢየሱስ አንዲያው የቀደመውን ሥርዓት እና ቤተክርስቲያን እንዲቀጥል ለማድረግ አለመምጣቱን የጠቀሱት በጥሩ ምክንያት ነው፡፡ በተመሳሳይም መንገድ፣ ኢየሱስ ሙሉ ለሙሉ አዲስ ቤተክርስቲያንም እንዳልመሠረተ መገንዘብም መልካም ነው፡፡ የእርሱ ቤተክርስቲያን የብሉይ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን አብይ ቅጥያ ናት፡፡

በወንጌላት እንደተመዘገበው ኢየሱስ ቤተክርስቲያንን ኤክሌሺያ በሚለው ስም የጠቀሳት በሦስት ጊዜያት ብቻ ነው፡፡ በመሠረቱም በማቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስና በዮሐንስ ከተመዘገበውም ኤክሌሺያ የሚለው ቃል የሚገኘው በዚህ ስፍራ ብቻ ነው፡፡ ሦስቱም ምንባቦች የሚገኙት በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ነው፡፡ አንዱ በማቴዎስ ምዕራፍ 16 ቁጥር 18 ሲሆን ሁለቱ ደግሞ በማቴዎስ ምዕራ 18 ቁር 17 ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እነዚህን ጥቅሶች በጥልቀት እንመልከታቸው፡

በማቴዎስ ማዕራፍ 16 ቁጥር 18 ኢየሱስ እንዲህ ተናገረ፡

> እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም። (ማቴ 16፥18)

በዚህ ስፍራ "እሠራለሁ" ተብሎ ነው የተተረጎመው ቃል፣ oikodomeo (አይኮዶሚዮ)፣ የሚያመለክተው አዲስን ነገር ስለ መገንባት ወይንም የነበረውን እንደገና አድሶ ስለ መገንባት የሚናገር ነው፡፡ ምንም እንኳን ኢየሱስ የትኛውን አገባብ እንደተጠቀመ ለይቶ ባይጠቅስም፣ በሮሜ ምዕራፍ 11 ጳውሎስ ያስተማረውን ትምህርት ስንመለከት ኢየሱስ የነበረው አመለካከት አስቀድሞ የነበረውን የብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያን አድሶ እንደሚገነባ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በማቴዎስ ምዕራፍ 18 ቁጥር 17 ኢየሱስ የተናገራቸው ቃላት እምብዛም አሻሚ አይደሉም፡፡ እስኪ የተናገረውን አድምጡ፡

> እነርሱንም ባይሰማ፥ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፤ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት፥ እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ። (ማቴ 18፥17)

በዚህ ጥቅስ፣ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ቤተክርስቲያን ስነ-ስርዓት ነው፡፡ የእርሱም ትዕዛዝ ንስሓ ያልገባ ሰው ወደ ቤተክርስቲያን ወይንም ወደ ማኅበሩ ሊመጣ የሚገባው መሆኑን ነው፡፡ በኢየሱስ አገልግሎት ወቅት የነበረው ብቸኛ ቤተክርስቲያን በተለያዩ ክልሎች ተበታትኖ የነበረውና በኢየሩሳሌም የነበረው የአይሁድ ምኩራብ ብቻ ነበር፡፡ እነዚያም ብሉይ ኪዳናዊው የእስራኤል ማኅበር ገፅታዎች ነበረ፣ ኢየሱስ ግን “ቤተ ክርስቲያን” ብሎ ይጠራቸዋል፡፡

ብሉይ ኪዳን እነዚህን መሳይ ፀቦች ብይን ሊሰጣቸው የሚገባው በሽማግሌዎች፣ በካህናትና በዳኞች ማለትም ፍርድን ለመበየን በተሾሙ የማኅበሩ ወኪሎች ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ይህንንም በዘፀአት ምዕራፍ 18፣ ዘዳግም ምዕራፍ 1 እና 19 ላይ እናገኛለን፡፡ ኢየሱስም በእርሱ ዘመን ይህንኑ መርህ ሲያፀናው፣ ፀቦቻቸውን በማኅበሩ ፊት በማቅረብ ማስወገድ እንዳለባቸው በማሳሰብ ነው፡፡ ኢየሱስ ግን ከዚያም ባሻገር አስቀድሞ በማቴዎስ ምዕራፍ 16 በጠቀሳት በእርሱ ቤተ ክርስቲያን ተግባራዊ ስለሚሆንበትም መንገድ ዒላማ አድርጎ ተናግሯል፡፡ ማቴዎስ የኢየሱስን ንግግሮች ያሰፈረልን ለዚህ ነው፡፡ በኢየሱስና በማቴዎስ ልቡና ውስጥ ያለው፣ ልክ በጳውሎስ ልቡና እንዳለው ሁሉ፣ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የብሉይ ኪዳኗ እስራኤል ማኅበር እድገት መሆኗን አስተዋላችሁን? ኢየሱስ እስራኤልን በቤተ ክርስቲያን ለመተካት አልመጣም፤ እስራኤልን በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ሊታደግና ሊያድስ እንጂ፡፡

በብሉይ እና በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያናት መካከል ያለውን ተከታታይነት ስንመለከት፣ ኢነዚህን ሁለት ቤተ ክርስቲያናት ከማስተሳሰር አንፃር ኢየሱስ የተጫወተውን ማዕከላዊ ድርሻ ማስተዋሉ አስፈላጊ ነው፡፡

በመጀመሪያ፣ ሰፋ ባለ አነጋገር፣ አዲስ ኪዳን ኢየሱስን የሚያቀርበው እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጠው ተስፋ ሙላት አድርጎ ነው፡፡ ሮሜ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 1 እስከ 4 እና ገላትያ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 16 እስከ 29 ስንመለከት፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን የጠበቀ እና ለአብርሃምና ለሙሴ እግዚአብሔር የተናገረውን የበረከት ተስፋ ሙሉ በሙሉ የወረሰ ታማኝ እስራኤላዊ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከሉቃስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 32 እና ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 31 እስከ 33 እንደምንማረው፣ ኢየሱስ የዳዊትን ዙፋን የሚያድስና በዳዊትም ዙፋን ላይ ተቀምጦ

በእስራኤልና በይሁዳ የሚገዛ የዳዊት ልጅ ነው፡፡ ኢየሱስ ካለፈው ነገር ጋር ጠብ የለውም፡፡ እርሱ የብሉይ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን ሙላቷ ሲሆን፣ እንከን አልባው አባቷና አገልጋይዋ ነው፡፡፡

ሁለተኛ፣ ኢየሱስ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን መሥራች፣ የወደቀችውን የብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያን ከወደቀችበት የሚያነሳ ተሃድሶን ያመጣ ነው፡፡  ቅዱሳት መጻሕፍት በኤፌሶን ምዕራፍ 5 ቁጥር 23 እና ቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 18 የቤተክርስቲያን ራስ ብለው ይጠሩታል፡፡ በኤፌሶን ምእራፍ 5 ከቁጥር 22 እስከ 33 እና ራዕይ ምዕራፍ 19 ከቁጥር 1 እስከ 10 የቤተክርስቲያን ባል ተብሎ ተጠቅሷል፡፡ በማቴዎስ ምዕራፍ 28 ከቁጥር 18 እስከ 20 በታላቁ ተልዕኮ ውስጥ የእርሱን ሥልጣን እንድትቀበል ቤተክርስቲያንን የሾመ ኢየሱስ ራሱ ነው፡፡ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን ይወዳል፣ ያፀናል ሥልጣንም ይሰጣል፡፡

> *የብሉይ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያላት ግንኙነት ከሥረ-መሠረቱ የአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ካላት ግንኙነት ጋር አንድ ዓይነት ነው፡፡ ለአንዳንድ ክርስቲያኖች፣ የብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ራሱ እንኳን በጣም እንግዳ ይሆንባቸዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የተወለደችው በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 እንደተጻፈው በበዓለ- ሃምሳ ቀን ነው ብለን ልናስብ እንችላለን፡፡ ግን ስለ ቤተክርስቲያን ስናስብ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን ያደረገላቸው የእርሱ ሕዝቦች፣ በጌታ በኢየሱስ ሥራ የተዋጁ የእግዚአብሔር ሕዝቦች አድርገን የምናስብ ከሆነ፣ እንግዲያው የብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያን ማለት መሲሁ አንድ ቀን ሲመጣ እግዚአብሔር የሚፈፅመውን ድነት የሚጠባበቁ አማኞች አካል ናት ማለት ነው፡፡ እናም ስለዚህ የብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ጸጋ፣ እግዚአብሔር በሚያፈስሰው፣ በመስቀል ላይ ኢየሱስ በሚያፈስሰው ደም ትታመናለች ማለት ነው፡፡ የብሉይ ኪዳን ክርስቲያኖች፣ የብሉይ ኪዳን አማኞች፣ የብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያን አባላት የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የተጠናቀቀ ሥራ በተስፋ ይጠባበቁ ነበር፡፡ ሁሉን በሁሉ በሆነ፣ የይገባኛል ጥያቄ በማይቀርብበት ኃጢአታቸውን አስወግዶ በእግዚአብሔር ፊት ባቆማቸው በእግዚአብሔር ጸጋና ምህረት ይታመኑ ነበር፡፡ ወደ ነገሩ ጉዳዩ ማዕከላዊ ሃሳብ ስንገባ፣ የብሉይ ኪዳን አማኞች እና የብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት እኛ እንደ አዲስ ኪዳን አማኞችና ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ግንኙነት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ [ዶ/ር ሳሙኤል ሊንግ]*

እስካሁን ድረስ፣ ስለ ቤተክርስቲያን ፈቃድ/ስምምነት የብሉይ ኪዳንን ዳራ በማንሳትና የኢየሱስን ምድራዊ አገልግሎት ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ፣ የእነዚህን ነጥቦች አንድምታዎች እንመለከታለን፡፡

# እንድምታዎች

ኢየሱስ የአዲስ ኪዳንን ቤተ ክርስቲያን የሾማት ለብሉይ ኪዳኗ እስራኤል ኅዳሴና እድገት መሆኑን ስንገነዘብ፣ የምናስተውለው አንድ ጠቃሚ አንድምታ በብሉይ ኪዳኗ እስራኤልና በአዲስ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን መካከል መሠረታዊ ቀጣይነት ያለ መሆኑን ነው፡፡ በተግባር ስንመለከተውም፣ የአዲስ ኪዳኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ ማኅበረሰብ የብሉይ ኪዳን ስሩን ሊያንፀባርቅ የሚገባው ሆኖ እናገኛለን፡፡ እርግጥ ነው፣ አንዳንድ ልዩነቶች ይኖራሉ፣ ስለዚህም አዲስ ኪዳን እነዚህን ለውጦች ሊያመለክት ይገባዋል፡፡ ግን አዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ከእስራኤል ጋር የቅርብ ተመሳሳይነት እንዳላትም ያስተምራል፡፡

የተከታታይነታቸው መግለጫ ነጥቦች ጠቅሰን የማንጨርሳቸው በርካቶች ናቸው፡፡ ከመካከላቸው ግን ሦስቱን ለመጥቀስ ጊዜ መውሰድ አግባብ ነው፡፡ አንደኛ፣ በብሉይ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያንና በአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን መካከል የዓላማ ተከታታይነት/ቀጣይነት አለ፡፡

# ዓላማ

የነገረ መለኮት ሊቃውንት የዓለምን ታሪክ በሦስት እርከኖች ያጠቃልሉታል፡ ፍጥረት፣ ውድቀትና መቤዠት፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እና 2 እንደተጠቀሰው፣ በፍጥረት እርከን፣ እግዚአብሔር ዓለምን፣ ተክሎችን፣ እንስሶችን እና የሰውን ዘር ፈጠረ፡፡ በአንድ ለየት ባለ የዓለም ክፍልም፣ የኤድን ገነትን ተከለ፡፡ ከእግዚአብሔር በተቀበለውም ሥልጣን፣ ምድርን መሙላትና መግዛት፣ የኤድንን ገነት ለአግዚአብሔር ቅዱስና የተገለጠ ኅላዌ የምትስማማ ማድረግ የሰው ዘር ኃላፊነት ነበር፡፡

በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 እንደተመዘገበው፣ በውድቀት እርከን ደግሞ፣ የሰው ዘር በእግዚአብሔር ላይ በማመፁ ከኤድን ገነት ተባረረ፡፡ የሰውም ዘር በኃጢአት ከመውደቁ የተነሳ፣ መላው ፍጥረት ረከሰ፡፡ ጳውሎስ ይህንን በሮሜ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 20 እስከ 22 አብራርቶታል፡፡

የተቀረው ታሪክ ደግሞ እግዚአብሔር የሰውን ዘር ወደ ቀደመው ክብሩ ለመመለስና በሰውም ዘር በኩል የተቀረውን ፍጥረት ወደ ቀደመው ያልተበረዘ ማንነቱ ለመመለስ የሠራው የመቤዠት እርከን ነው፡፡ የመቤዠት ዘመን የመጨረሻው እርከን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር መፈጠራቸው ነው፡፡ ይህንንም በኢሳያስ ምዕራፍ 65 ቁጥር 17 እና 66 ቁጥር 22፤ 2ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 13 እና ራዕይ ምዕራፍ 3 ቁጥር 13 ላይ እናነባለን፡፡ ይህ የሰው ዘርና የፍጥረት መቤዠት በሁለቱም ኪዳናት ውስጥ ዘወትር የእግዚአብሔር ዓላማ ሆኖ ዘልቋል፡፡

በዘመነኛው ዓለም፣ ቤተክርስቲያን አሁንም ይህንን የፍጥረት ኀዳሴ ከግብ ለማድረስ እየተጋች ነው፡፡ የአዲስ ኪዳን አስተምህሮ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ነገሮች በመቀጠልም፣ ወንጌልን በተቀዳሚነት በመስበክ፣ ወደ ክርስቶስ የመጣ ሰው ሁሉ ወደ መጨረሻው የመቤዠት እርከን የሚደረገውን ግስጋሴ የሚወከል መሆኑን በማወቅ ይህንን ተግባር እንፈፅማለን፡፡ በተጨማሪም በዓለም ላይ እንደ ክርስቲያኖች በመኖር፣ የክርስቶስን ፍቅር ለጎረቤቶቻችን በማሳየት እና በዙሪያችን ያለው ባህል እግዚአብሔርን የሚያከብር ግርማውንና ባህርዩን የሚገልጥ እንዲሆን ለመለወጥም እንተጋለን፡፡ ይህንንም ኢየሱስ ተመልሶ በመምጣት የመቤዠት ሥራውን የሚያጠናቅቅባትን ቀን በጸሎትና በተስፋ እንጠባበቃለን፡፡

በአሁኑ ዘመን የብሉይ ኪዳን ቤተ ክርስቲያንና የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ተከታተይነት/ቀጣነት ሁለተኛ ነጥብ ሁለቱም የእግዚአብሔር ጉባኤዎች አማኞችንም የማያምኑትንም የሚያካትቱ መሆናቸው ነው፡፡

# አማኞችና አማኝ ያልሆኑ

በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን፣ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ፍፁም አልነበረችም፡፡ በብሉይ ኪዳን፣ ጥቂት የጥንት እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ታማኝ ነበሩ ከእግዚአብሔርም በረከትን ተቀብለዋል፡፡ በርካታ የሆኑት ሌሎቹ ግን ባለማመን የእግዚአብሔር ጣላቶች ሆነው ቆሙ ስለዚህም በመለኮታዊ ፍርድ ስር ወደቁ፡፡ ይህንንም በብሉይ ኪዳን ከጫፍ እስከ ጫፍ እንመለከታለን፣ በዘሌዋውያን ምዕራፍ 26 እና በዘዳግም ምዕራፍ 27 እስከ 30 እንደምናገኘው ግን የእግዚአብሔር ኪዳን የሚያስከትላቸው በረከቶችና መርገሞች በግልፅነት ጠቅለል ብለው ተቀምጠዋል፡፡

በተመሳሳይም መንገድ ይኸው ነገር ለአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያንም ማለትም የክርስቶስ ተከታይ ለሆነው ጉባኤም እውነትነት አለው፡፡ በየቤተ ክርስቲያኖቻችን አማኞችንና የማያምኑትን በአንድነት እናገኛለን፡፡ ለአብነት ያህል፣ ይሁዳ ከሐዋርያቱ መካከል ታማኝ ያልሆነ ነበር፡፡ ይህም ነገር በዮሐንስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 70 እና 71 ላይ ተመዝግቧል፣ ኢየሱስንም አሳልፎ በሰጠባት ወቅትም ታይቷል፡፡ በራዕይ ምዕራፍ 2 እና 3 ላይ ለአብያተ ክርስቲያናት በተፃፈው ደብዳቤ ውስጥም ይኸው የቤተክርስቲያን ድብልቅ ገፅታ በገሃድ ይታያል፡፡ እነዚህ የራዕይ ምዕራፎች እውነተኞቹ አማኞች እነዚህን ሁኔታዎች ድል መንሳት እንደሚገባቸው ያሳስባሉ፡፡ ድል መንሳት የተሳናቸው ግን የማያምኑት ሰዎች ኢ-ተአማኒነት ሊጋባባቸው እንደሚችል ያስጠነቅቃል፡፡ የ1ኛ ዮሐንስ መልእክት አብዛኛው ክፍል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን አማኞችና የማያምኑትን መለየትን ዒላማ ያደረገ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ በርካታ ምንባቦች በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ የሃሰት

አስተማሪዎችን የሚያስጠነቅቁ ሲሆን፣ እምነታቸውንም እስከ መጨረሻው አፅንተው የሚይዙትንም ያበረታታሉ፡፡

በ2ኛ ቆሮንቶስ ምእራፍ 13 ቁጥር 5 ላይም፣ ጳውሎስ ይህንን እውነት እውቅና ይሰጠዋል፣ ሰዎችም ይህንኑ እንዲያፀኑ ያበረታታል፡፡ እስኪ የፃፈውን አድምጡ፡

> በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ፤ ወይስ ምናልባት የማትበቁ ባትሆኑ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ እንዳለ ስለ እናንተ አታውቁምን? (2ቆሮ 13፥5)

የቤተ ክርስቲያን አባልነት፣ ጥምቀት፣ ዋጋ የሚሰጠው የእምነት መግለጫ የመሳሰሉት ነገሮች ብቻቸውን በኢየሱስ ክርስቶስ ለሆነውና ለሚያድነው እምነት እርግጠኛ ምልክቶች ተደርገው መወሰድ እንደሌለባቸው ሰው ሁሉ እንዲገነዘብ ጳውሎስ ይፈልጋል፡፡ በክርስቶስ ወደ ሆነው እምነት ያልመጡ ሰዎችም እነዚህን ነገሮች ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህ በቤተክርስቲያን ያሉ ሰዎች ራሳቸውን እንዲመዝኑ፣ ለድነታቸውም በእውነት በክርስቶስ የታመኑ መሆናቸውን እንዲያረጋግጡ ጳውሎስ ያበረታታል፡፡

እርግጥ ነው፣ እንደ ሰብዓዊ ፍጡራን የሌላውን ሰው ልብ ሁኔታ ልናውቅ አንችልም፡፡ እንቅስቃሴያቸውን ብቻ እናያለን ቃሎቻቸውንም ብቻ እንሰማለን፡፡ ስለዚህም፣ እውነተኛዎቹ አማኞች የትኞቹ እንደሆኑ መናገር አንችልም፡፡ ግን በማኅበረ ምዕመናኖቻችን ውስጥ ያላመኑ ሊኖሩ እንደሚችሉ ማወቃችን ራሳችንንና ሌሎችን የምናይበትን ዕይታ መነካካቱ አይቀርም፡፡ ስለዚህ በእርግጠኝነት እነማን እንደሆኑ ባናውቅም ያላመኑትን ሰዎች ወደ እምነት ለማምጣት በቤተክርስቲያኖቻችን ለሁሉም ሰው ወንጌልን መስበክና ማስተማራችንን ልንቀጥል ይገባናል፡፡ ምንም እንኳን በክርስቶስ በይፋ ማመናቸውን ባይገልጡም ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይመጡ መከልከል የለብንም፣ በአንድም በሌላም መንገድ እግዚአብሔርን የሚሹትን ልንቀበል ይገባናል፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለረጅም ዘመናት የቆዩ ቢሆኑም እንኳን ከእምነትና ከብስለት አንፃር በርካታ መለያየቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ ሌሎችን በልበ ሰፊነት በትዕግሥት መያዝ ይገባናል፡፡

በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያኖች መካከል ያለው ሦስተኛው ቀጣይነት ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት ግዴታ ያለባቸው መሆኑ ነው፡፡

# ግዴታዎች

በሁለቱም ኪዳናት ውስጥ ያሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርን የመውደድ፣ መንግሥቱን በዓለም ሁሉ የማስፋት እና ለእርሱ ክብርን የማምጣት ሃላፊነት ተሰጥቷቸዋል፡፡ እግዚአብሔርን ከመውደድ አንፃር፣ ዘዳግም ምዕራፍ 6 ቁጥር 5 እና 6 እንደሚያስተምረን የብሉይ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን በፍፁም ልብ ልትወድድ፣ ሕጉንም በፍፁም ልብ ልትፈፅም ይገባት ነበር፡፡

በተመሳሳይም መንገድ፣ የአዲስ ኪዳንም ቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን እንድትወድድና ሕጉንም እንድትጠብቅ ተጠርታለች፡፡ ኢየሱስ በማቴዎስ ምዕራፍ 22 ቁጥር 37 እንዳስተማረው፣ ከሕግ ሁሉ የሚልቀው ከልብ እግዚአብሔርን መውደድ ነው፡፡ በ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 3 ዮሐንስ ለእግዚአብሔር ያለን ልባዊ ፍቅር ሕግጋቱን ከልባችን እንድንታዘዝ ያስችለናል በማለት ያስተምራል፡፡

> *ተደጋግመው ከሚጠየቁ ጥያቄዎች መካከል አንዱ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የብሉይ ኪዳንን ሕግ ልትጠብቅ ይገባታል ወይ? የሚለው ነው፡፡ መልሱም ይገባታልም አይገባትምም የሚል ነው፡፡ አይገባትም ስንል በብሉይ ኪዳኑ ቶራ ላይ የተሰጡ አንዳንድ ድንጋጌዎች በእርግጥ ስለተነሱልን ነው፡፡ ለምሳሌ ልጆቻችንን መግረዝ የጌታ የመሆን ያለመሆናችን ምልክት አይሆንም፡፡ በዓመት ሦስት ጊዜ ወደ መቅደስ መሄድ አይጠበቅብንም፡፡ እንዲህ እንዲህ ያሉትን ዝርዝሮቹን መመልከት እንችላለን፡፡ በመሠረቱ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 በኢየሩሳሌም ተሰብስቦ የነበረው ጉባዔ የተወያየውም በዚሁ ጉዳይ ነበር፡፡ ሆኖም ግን የብሉይ ኪዳኑ ቶራ ዓላማው ምን ነበር? ቶራ የእግዚአብሔርን ማንነትና ባሕርይ ለእኛ ከመግለጡ አንፃር ያንንም ማንነት እና ባሕርይ እኛ እንድንጋራው የሚጠበቅብን ከመሆኑ አንፃር፣ ቶራ አሁንም ይሠራል፡፡ እንደማስበውም ይህንን በጳውሎስ ደብዳቤዎች ውስጥ ትመለከቱታላችሁ፡፡ ጳውሎስ ለአንባቢዎቹ፡ "አይደለም፣ ነፃ ናችሁ፡፡ እነዚህን ሁሉ የመፈጸም ግዴታ የለባችሁም፡፡ ምንም እንኳን ነፃ ብትሆኑም ግን፣ አትዋሹም፣ አትቀኑም ደግሞም አታመነዝሩም" ይላቸዋል፡፡ እንግዲያው ታዲያ፣ ለድነታችን ቶራን መጠበቅ ይገባናልን? በፍፁም፡፡ ግን እንዲያው የዳኑ ሁሉ፣ እግዚአብሔራዊ የሆነውን ሕይወት እንዲያሳዩ ይጠበቅባቸዋል ወይ? አዎን፡፡ [ዶ/ር ጆን ኦስዋልት]*

በሁለቱም ኪዳናት የነበሩ የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔርን መንግሥት ያስፋፉ እንደነበር ልብ በሉ፡፡ የብሉይ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን በዘፍጥረት ምእራፍ 17 ቁጥር 4 እና 5፣ እግዚአብሔር አብርሃምን የብዙ ሕዝብ አባት አደርግሃለሁ ብሎ የሰጠውን ተስፋ ታውቃለች፡፡ በሮሜ ምእራፍ 4 ቁጥር 13 ጳውሎስ እንዳስተማረው፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት በዓለም ሁሉ ላይ ማስፋት

የእምነት ግዴታዋ መሆኑን የብሉይ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ታውቅ ነበር፡፡ በተመሳሳይም መንገድ ኢየሱስም ቤተ ክርስቲያኑን እንዳዘዘው፡

እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ በማወጅ ይህንን ዕቅድ ተግባራዊ ታደርጋለች፡፡

የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የሚጋሩት ሦስተኛ ግዴታ እግዚአብሔርን ማክበር ነው፡፡ የብሉይ ኪዳንን በተመለከተ በመዝሙር 86 ቁጥር 12 እና 115 ቁጥር 18 ላይ የምንመለከተው ሲሆን፣ በአዲስ ኪዳንም ስለ ብሉይ ኪዳን በተሰጠው መግለጫ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 17 ከቁጥር 24 እስከ 28 ውስጥ እናየዋለን፡፡ ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 27 እንደሚያስተምረንም፣ በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠራችንም ይህንኑ ይገልጣል፡፡ በብሉይ ኪዳን ዓለም ውስጥ፣ ሰዎች ንጉሣቸውን እንዲወድዱ፣ እንዲታዘዙና እንዲያከብሩ ለማሳሰብ የነገሥታት ምስሎች ያሉባቸው ሃውልቶች ይቆማሉ፡፡ የሰውም ዘር እንደ እግዚአብሔር አምሳልነቱ፣ ለእግዚአብሔር ክብርን ያመጣ ዘንድ የተሠራ ነው፡፡

በተመሳሳይም መንገድ፣ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያንም እግዚአብሔርም ማክበር ይጠበቅባታል፡፡ ይህንንም በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 10 ቁጥር 31፣ በ1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 4 ቁጥር 11 እና በራዕይ ምዕራፍ 4 ቁጥር 11 እና በሌሎችም በርካታ ስፍራዎች እናገኘዋለን፡፡

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው ሃላፊነት ጫና አይደለም፡፡ ጫና የማይሆነው ግን በክርስቶስ ስንሆን ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፊት በራሳችን ብቃት ለመቆም ከሞከርን፣ ግዴታዎቻችን ደፍጥጠው ይጨርሱን ነበር፡፡ በክርስቶስ ግን፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ እውነተኛ አማኞች ከኩነኔ ነፃ ናቸው፣ የጌታን መንግሥት ከማስፋት አንፃር ለመንቀሳቀስ ብቃት አላቸው፣ ያለ አንዳች የውድቀት ፍርሃትም ሕጉን ለመጠበቅ፣ ለእርሱም ክብርን ለማምጣት ይችላሉ፡፡ በመሠረቱ፣ ስኬታማነት የተረጋገጠ ነው፡፡ ምንም እንኳን ጊዜያዊ መሰናክሎች ቢገጥሙንም፣ ታሪክ ግን ከእግዚአብሔር ድል አድራጊነት አንፃር ይጓዛል፡፡ ይህም በቤተክርስቲያን በኩል ይስፋፋል፡፡ ስለዚህ፣ እጅግ በታዘዝን መጠን ግዴታዎቹንም ይበልጥ እንፈፅማለን ያን ጊዜም እግዚአብሔር መንግሥቱን ወደ ፍፃሜው የከበረ ሙላት ያፋጥነዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን በብሉይ ኪዳን የነበራትን የመነሻ እርከንና በአዲስ ኪዳንም በክርስቶስ በተረጋገጠው አካል ውስጥ መገለጡን በመመልከት፣ ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ፈቃድ/ ስምምነት የተመሠረተች መሆኑ ግልፅ ሆኖልናል፡፡ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር እንድትኖር ስለሚፈልግ ትኖራለች፣ ምክንያቱም የእርሱን ዓላማ ታስፈፅማለችና ነው፡፡ እርሷም በእግዚአብሔር የተወደደች፣ ለአገልግሎቱና ለክብሩም የተለየች ሙሽራውና አካሉ ናት፡፡

ይህንን የቤተክርስቲያንን የመለኮት ፈቃድና/ስምምነት በልቡናችን ይዘን፣ ወደ ሁለተኛው ርዕሳችን እንሻገራለን፡፡ ያም ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ናት የሚለው ነው፡፡

# 3. ቅዱስ

በመጽሐፍ ቅዱሳችን፣ ቅድስና የሚለው ሃሳብ በተለያዩ ቃላት ተገልጦ እናገኘዋለን፡፡ በአዲስ ኪዳን፣ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ወይም የተቀደሰች ተብላ ተገልጣለች፡፡ በቤተክርስቲያን ያሉ ሰዎችም ቅዱሳን ተብለው ተጠርተዋል፡፡ እነዚህ ሦስቱ ቅዱስ፣ የተቀደሰና ቅዱሳን የሚሉ ቃላት ከአንድ የግሪክ ቃል የወጡ ናቸው፡፡ “ቅዱስ” የሚለው ቃል hagios የሚለው ቅጽል ፍቺ ሲሆን፣ “የተቀደሰ” የሚለው ደግሞ hagiazo የሚለው ግስ ፍቺ ነው፡፡ ያም ማለት ቅዱስ የተደረገ ማለት ነው፡፡ “ቅዱሳን” የሚለው ስም ደግሞ hagios የሚለውን ስም፣ ማለትም ቅዱስ የሆነ የሚለውን ይፈታል፡፡

በብሉይ ኪዳን፣ ተመሳሳዮቹ ሃሳቦች በተለያዩ የዕብራይስጥ ቃላት ተገልጠዋል፡፡ ለምሳሌ qadosh, የሚለው ቅፅል ቅዱስ ማለት ሲሆን፣ qadash, የሚለው ደግሞ መቀደስ የሚል ፍቺ ይይዛል፡፡ qodesh የሚለው ደግሞ ቅዱሳን የሚለውን ይይዛል፡፡

ስለ ቅድስና ስንነጋገር፣ ብዙ ክርስቲያኖች ቅድስና እግዚአብሔርን ከፍጥረቱ የሚለየው ነገር ነው ብለው ያስባሉ፡፡ የእግዚአብሔር ቅድስና የእርሱ ማንነት ከማንም ጋር የማይገጥም ወይም ከፍጥሩ የተለየ መሆኑን የሚያመለክት ነው ይባላል፡፡ ግን “ቅዱስ” የተሰኘው ቃል በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጠው በዚህ መንገድ ብቻ አይደለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቅድስና የሚያንጸባርቁ ፍጥረታትን ወይንም አንዳንድ ዕቃዎችን ቅዱስ ይላቸዋል፡፡ በዚህም ረገድ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ናት ይላል፡፡

ቤተክርስቲያን ቅዱስ ናት የሚለውን ሃሳብ በሁለት ክፍሎች እንመለከታለን፡፡ አንደኛ፣ “ቅዱስ” የሚለውን ቃል ፍቺ እንፈልጋለን፡፡ ሁለተኛ፣ ይህንንም ፍቺ ቅዱስ የሆነውን ሕዝብ ለመለየት እንጠቀምበታለን፡፡ እስኪ ስለ ቅድስና መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ፍቺ በመመልከት እንጀምር፡፡

## ትርጓሜ

በቅዱሳት መጻሕፍት፣ ቅድስና የሚለው ሃሳብ ውስብስብ ነው፡፡ ግን መጽሐፍ ቅዱስ አንድን ሰው ወይንም ነገር ቅዱስ ብሎ ካቀረበው፣ መሠረታዊው ሃሳብ ተጠቃሹ በግረገብ ንፁህ ነው ማለት ሲሆን፣ በተዛማጅነትም፣ "ቅዱስ" ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተለዩ ሰዎችን ወይንም ነገሮችን ሊያመለክት ይችላል፡፡

የዚህን ፍቺ ሁለት ገጽታዎች፣ አስቀድመንም ስለ ግብረገባዊ ንፁሕነት እንመልከት፡፡ አንድ ሰው ወይንም ነገር ግብረገባዊ ንፁህ ነው ስንል፣ ከኃጢአትና ከርኩሰት የጸዳ ነው ማለታችን ነው፡፡ ከግብረገባዊ ንፅሕና አንፃር፣ የቅድስና ስሩ የእግዚአብሔር ባህርይ ይሆናል፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔርን ቅዱሱ በማለት በበርካታ ስፍራዎች ይገልጡታል፡፡ ለምሳሌ፣ 2ኛ ነገሥት ምዕራፍ 19 ቁጥር 22፣ ምሳሌ ምዕራፍ 9 ቁጥር 10፣ ኢሳያስ ምዕራፍ 30 ከቁጥር 11 እስከ 15 እና 1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 20 ይጠቀሳሉ፡፡

> *ነገሩ እግዚአብሔር ከእኛ በላይ ትልቅ ነው የምንለው ዓይነት ብቻ አይደለም፤ እግዚአብሔር የማይገደብ እኛ ግን የተገደብን ነን የምንለውም ብቻ ዓይነትም አይደለም ግን እርሱ ከእኛ በግረገባዊነት እጅግ ልዩ ነው ማለት ነው፡፡ በእርሱ ዘንድ ጨለማም በመዞርም የሚገኝ ጥላ የለም፡፡ በእርሱ ዘንድ የክፉ ግፊትም ሆነ ወደ ተሳሳተ ነገር የማዘንበል ነገርም የለም፡፡ በእርሱ ዘንድ ክፉን የማድረግ ጥቂት ፍንጭ እንኳን የለም፡፡ [ዶ/ር ጄ. ሊዮን ዱንካን ሳልሳዊ]*

እግዚአብሔር ፍፁም ቅዱስ ከመሆኑ የተነሳ፣ በእርሱ መገኘት ውስጥ የሚገኝ የትኛውም የኃጢአት ድርጊት የእርሱ ፍርድና ቁጣ ያርፍበታል፡፡ ይህንንም 1ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 6 ቁጥር 20፣ 2ኛ ነገሥት ምዕራፍ 24 ቁጥር 3 እና ዕብራውያን ምዕራፍ 12 ቁጥር 14 ላይ እንመለከታለን፡፡ ምንም እንኳን እግዚአብሔር ፍርዱን ለጊዜው ቢያዘገየውም፣ የእርሱ በቅድስናው መገለጥ ኃጢአታቸው ያልተሸፈነላቸውን በፍፃሜው ማጥፋቱ አይቀሬ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ማንም ሰው ወይንም ነገር ወደ እርሱ መገኘት ከመግባቱ አስቀድሞ ሊቀደስ ይገባዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በኢሳያስ ምእራፍ 6 ከቁጥር 3 እስከ 7 ኢሳያስ የተናገረውን አስተውሉ፡

> አንዱም ለአንዱ። ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
> ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበር።
> የመድረኩም መሠረት ከጭዋኺው ድምፅ የተነሣ ተናወጠ፥ ቤቱንም ጢስ
> ሞላበት።
> እኔም። ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ፥ ከንፈሮቻቸውም
> በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል በመቀመጤ ዓይኖቼ የሠራዊትን ጌታ

ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ! አልሁ።
ከሱራፌልም አንዱ እየበረረ ወደ እኔ መጣ፥ በእጁም ከመሠዊያው
በጉጠት የወሰደው ፍም ነበረ።
አፌንም ዳሰሰበትና። እነሆ፥ ይህ ከንፈሮችህን ነክቶአል በደልህም ከአንተ
ተወገደ፥ ኃጢአትህም ተሰረየልህ አለኝ። (ኢሳ 6፥3-7)

በዚህ ምንባብ፣ ኢሳያስ በቅዱሱ ጌታ ህልውና ውስጥ ሲገኝ በበደሉ ወይንም በኃጢአቱ ምክንያት እጠፋለሁ ብሎ እንደፈራ እንመለከታለን፡፡ ስለዚህም፣ ከሱራፌል አንዱ መልአክ፣ ከእግዚአብሔር የተቀደሰ መሰዊያ በጉጠት በወሰደው እሳት ኃጢአቱን አነፃለት፡፡ በዚህም የማንጻት ሥራ፣ ኢሳያስ ከኃጢአት ነፃ፣ ተቀደሰም፡፡ ባገኘውም አዲስ ቅድስና ምክንያት ከፍርድ አምልጦ በእግዚአብሔር ህልውና ውስጥ መገኘት ቻለ፡፡

በኢሳያስ ምዕራፍ 6 እንደተመለከትነው፣ የእግዚአብሔር ቅድስና ከእግዚአብሔር ተግባቦታዊ የባህርይ መገለጫዎች አንዱ ነው፡፡ ያም ባህርዩ በፍፅምናና በሙላት ይገለጠዋል፡፡ የእርሱም ፍጥረታት በተወሰነ መጠን የሚገለጡበት ይሆናል፡፡  የቅድስና ተሸጋጋሪ ተፈጥሮ አማኞች እንዲቀደሱ ከተሰጧቸው በርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዛት ጀርባ የሚያርፍ ነው፡፡ ይህንም በኤፌሶን ምዕራፍ 1 ቁጥር 4፣ ዕብራውያን ምዕራፍ 12 ቁጥር 14 እና 1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 15 እና 16 እናገኘዋለን፡፡ እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ መቀደስን ልንናፍቀው ይገባል፡፡ እርግጥ ነው፣ ይህንን መሻት በራሳችን ብርታት ከግብ ልናደርሰው አንችልም፡፡ ግን ክርስቶስ ግብረገባዊ ንፅህናው የተጠበቀ እንደነበር እናውቃለን፡፡ እኛም በእርሱ ስንሆን፣ የእርሱ ጽድቅ የእኛ ሆኖ ተቆጥሮልናል፣ እኛም ፍጹም ቅዱሳን ሆነን ተቆጥረናል፣ ከኃጢአትና ከርኩሰትም ነፅተናል፡፡

ቅዱስ የተሰኘው ቃል ሁለተኛ ፍቺያችን ለእግዚአብሔር የተለየ አገልግሎት የተለዩ ሰዎችንና ነገሮችን ለመግለጥ የምንጠቀምበት ነው፡፡ በዚህ ረገድ፣ ነገሮች ምንም እንኳን በራሳቸው ግብረገባዊ ንፁሐን ባይሆኑም ይቀደሳሉ ማለታችን ነው፡፡ አንድ ምሳሌ ለማንሳት፣ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 7 ቁጥር 14 የጻፈውን አድምጡ፡

ያላመነ ባል በሚስቱ ተቀድሶአልና፥ ያላመነችም ሚስት በባልዋ ተቀድሳለች፤ አለዚያ ልጆቻችሁ ርኩሳን ናቸው፤ አሁን ግን የተቀደሱ ናቸው። (1ቆሮ 7፥14)

ጳውሎስ በዚህ ስፍራ፣ አማኝ ያላመነ ካገባ፣ የማያምነው ተቀድሷል፣ ወይንም አንዳንድ ትርጉሞች እንደሚያስቀምጡት፣ የማያምነው “ይቀደሳል”፡፡ ሃሳቡም ምንም እንኳን የማያምነው ሰው በክርስቶስ አማካይነት በእግዚአብሔር የነጻ ባይሆንም ከእግዚአብሔር ጋር እንዲተዋወቅና ለእርሱም የሚጠቅም ሊደረግ ይችላል ማለት ነው፡፡

አንዳንድ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር እንከን ያለባቸውንና ንፁህ ልሆኑ ሰዎችን ለአገልግሎቱ የመለየቱ ነገር እንግዳ ይሆንባቸዋል፡፡ ግን ስለ ነገሩ ረጋ ብለን ስናስብ፣ እግዚአብሔር ፍቃዱን ያስፈፅምባቸው ዘንድ ስለለያቸው የማያምኑ ሰዎች በርካታ ምሳሌዎችን መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠን ሆኖ እናገኛለን፡፡ ምናልባትም ዋነኛ ምሳሌ ሆኖ የምናገኘው ጌታችንንና አዳኛችንን ኢየሱስ ክርስቶስን አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ሊሆን ይችላል፡፡ ኢየሱስ ራሱ እንዳስተማረውም ፣ ይሁዳ ለዚያ ዓላማ ተመርጧል፡፡ የእርሱ አሳልፎ መስጠትም ለእግዚአብሔር ከቀረቡት መስዋዕቶች ሁሉ እጅግ የተቀደሰው መስዋዕት - በብርቅዬ ልጁ ሞት እንዲቀርብለት ሆኗል፡፡ እግዚአብሔር ለአገልግሎቱ በደለኛ አላማኞችን እንኳን የሚጠቀም ከሆነ፣ በሚወዱትና በተቀደሱ ልጆቹ ልዩ አገልግሎትማ ምንኛ የበለጠ ይከብር ይሆን?

እንደተመለከትነው፣ የቅድስና ሃሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠነ ሰፊ አድማስ አለው፡፡ ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት “ቅዱስ” ወይም “የተቀደሰ” ወይም “ቅዱሳን” የሚሉትን ቃላት ለቤተክርስቲያን መግለጫነት ሲጠቀሙ ምን ማለት እንደፈለጉ ለመረዳት ጠንቃቃ ልንሆን ይገባል፡፡ አንዳንድ ጊዜ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በቤተክርስቲያን የሚኖሩ አማኞች ከተሰጣቸው የክርስቶስ ቅድስና የተነሳ ግብረገባዊ ንፁሃን ናቸው ወደሚለው እውነታ ትኩረትን ለመሳብ ይጠቀሙበታል፡፡ በሌላ ወቅት ደግሞ፣ ምንም እንኳን እውነተኛ አማኞች ባይሆኑም ለእግዚአብሔር የተቀደሰ አገልግሎት ከዓለም የተለዩትን ለማመልከት ይጠቀሙበታል፡፡ በአንዳንድ ጉዳዮችም፣ እውነተኛ አማኞች ለእግዚአብሔር የተቀደሰ አገልግሎት የተለዩ ናቸው የሚለውን ሃሳብ ለማመልከት ይጠቀሙበታል፡፡

ምንም ይሁን ምን፣ ቅዱስ የሆነ የትኛውም ነገር ወይም የትኛውም ሰው ለእግዚአብሔር የተለየ መሆኑን እናውቃለን፡፡ የእግዚአብሔር ስም ቅዱስ ነውና፣ በከንቱ አንጠራውም፣ ይልቁኑ እናከብረዋለን፡፡ ለመጽሐፍ ቅዱስም እንገዛለን ምክንያቱም የተቀደሰው አምላካችን ቅዱስ ቃል ነውና፡፡ በሕይወታችን የትኛውም ገፅታ፣ ጌታ ለተቀደሰ ሕይወት የጠራን መሆኑን በማወቅ ግብረገባዊ ንፅህናን የምንናፍቅ እንሆናለን፡፡ በእርሱ ቅዱስ ቤተክርስቲያንም ውስጥ በመሰጠት እንሳተፋለን፡፡ ቅድስናን በምናገኝበት ስፍራ ሁሉ፣ የእግዚአብሔር እጅ እንዳለች እንረዳለን፣ እናም አምላካዊ ከበሬታ በሚሰጥ መንገድም አክብረን እንይዘዋለን፡፡

“ቅዱስ” ለሚለው ቃል የሰጠነውን ፍቺ በልቡናችን ይዘን፣ ከዚህ በመቀጠል ቅዱስ የሆኑ ሰዎችን ማንነት ለመዳሰስ እንጠቀምበት፡፡

# ህዝብ

ሰፋ ባለ መንገድ ለመናገር፣ እግዚአብሔር ሰዎችን “ቅዱስ” ብሎ የሚጠራቸው ለእግዚአብሔር የተቀደሰ አገልግሎት ከተቀረው ዓለም የተለዩ መሆናቸውን ለማመልከት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የብሉይ ኪዳኗ የእስራኤል መንግሥት በመደበኛነት “ቅዱስ” ተብላ ትጠራ ነበር ምክንያቱም እግዚአብሔር እንደ መንግሥት ከእርሷ ጋር ኪዳን ገብቶ ነበርና ነው፡፡ ይህንንም በዘፀአት ምዕራፍ 19 ቁጥር 5 እና 6፣ ዘዳግም ምዕራፍ 7 ከቁጥር 6 እስከ 9፣ ምዕራፍ 28 ቁጥር 9 እና ሕዝቅኤል ምዕራፍ 37 ከቁጥር 26 እስከ 28 በመሳሰሉት ክፍሎች እንመለከታለን፡፡

ይህም መሪ ቃል በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያንም ቀጥሎ እናገኘዋለን፡፡ ለምሳሌ፣ሉቃስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 72 ኢየሱስ የመጣው የእግዚአብሔርን የተቀደሰ ኪዳን ለማስፈፀም እንደሆነ ይናገራል፡፡ እናም ቤተ ክርስቲያን የታደሰችውና እንደገና የተገነባችው የአዲሱ ኪዳን እስራኤል ስለሆነች ቅዱስ ተብላ ተጠርታለች፡፡ ይህንንም በቆላስይስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 12፣ ዕብራውያን ምዕራፍ 10 ቁጥር 29 እና በሌሎችም በርካታ ስፍራዎች እንመለከተዋለን፡፡ አንድ ምሳሌ ለመውሰድ፣ በ1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 9 ለአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን የተናገረውን አድምጡ፡

> እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤ (1ጴጥ 2፥9)

በዚህ ስፍራ፣ ጴጥሮስ ስለ እስራኤል ቅዱስነት የሚናገሩ በርካታ የብሉይ ኪዳን ምንባቦችን ያጣቀሰ ሲሆን ከቤተክርስቲያን ጋር አዛምዶ አቅርቧቸዋል፡፡ ነጥቡም በሁለቱም ኪዳናት ውስጥ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን አንድና ተመሳሳይ የተቀደሰ ህዝብ ናት የሚል ነው፡፡

እንደተመለከትነውም፣ በእስራኤልም ሆነ በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን የሚገኝ እያንዳንዱ ሰው ሁሉ እውነተኛ አማኝ አይደለም፡፡ ሆኖም ግን፣ ሁሉም የተቀደሱ ተብለው ተጠርተዋል ምክንያቱም የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ማኅበረሰብ አባል ናቸው፣ ያም ማለት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ያላቸው ህዝቦች ናቸው ማለት ነው፡፡

በቃል ኪዳን ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ አማኞች፣ ቅድስናቸው ከማያምኑት ቅድስና እጅግ የላቀ ነው፡፡ የማያምኑት የተቀደሱት ለእግዚአብሔር የተለዩ ስለነበሩ ብቻ ነው፡፡ የሚያምኑት ቅዱስ የሆኑት ግን ለእግዚአብሔር የተለዩ ስለሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በክርስቶስ በመሆናቸው ምክንያት ለግብረገባዊ ንፅህና እና እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ራሳቸውን የሰጡ ስለሆኑም ነው፡፡ እርግጥ ነው፣ ላዕላይ ግቡ የቃልኪዳኑ ማኅበረሰብ በጠቅላላ እንዲያምን ነው፡፡ ማለትም እያንዳንዱ ሰው ለእግዚአብሔር የታመነና የተቀደሰ ሕይወትን እንዲኖር ማለት ነው፡፡

ስለተቀደሰው ህዝብ ከማሰብ አንፃር የሚረዳን አንዱ መንገድ በምትታየዋና በማትታየዋ ቤተክርስቲያን መካከል ባለው ትውፊታዊ መለያ ውስጥ ይገኛል፡፡ ከምትታየዋ ቤተክርስቲን በመጀመር፣ ሁለቱንም ጎራዎች እንመልከታቸው፡፡

## የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን

> *የምትታየዋ ቤተክርስቲያን የሚያመለክተው የምናያትን ቤተ ክርስቲያን ነው፣ በዚህም ረገድ በግልፅ ትታያለች ማለት ነው፡፡ እንግዲህ የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን፣ በመላው ዓለም ቤተ ክርስቲያን ብለው ራሳቸውን የሚጠሩትን የምታካትት ናት፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደሚከተሉ፣ በአሁኑም ዓለም የእግዚአብሔርን ዓላማ ዓላማቸው እንደሚያደርጉና ቃሉንም መመሪያቸው እንደሚያደርጉ የሚያውጁ ቤተእምነቶችን ሁሉ ማለት ነው፡፡ ይህም በርካታ ቤተእምነቶችን፣ ከየትኛውም ቤተ እምነት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸው ግን ራሳቸውን እንደ ክርስቶስ ተከታይ የሚቆጥሩትን ሁሉ ሊያካትት ይችላል፡፡ [ዶ/ር ማርክ ስትራውስ]*

በየትኛውም ዘመን፣ የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በመደበኛነት በሚሰበሰቡ ጉባኤዎች የሚካፈልን የትኛውንም ሰው፣ የልቡ ሁኔታ ምንም ይሁን ምን በውስጥዋ አካትታ ትይዛለች፡፡ ሰዎች የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አካል የሚሆኑባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ በአዲስ ኪዳን በጥምቀት፣ በብሉይ ኪዳን ደግሞ በመገረዝ የእግዚአብሔር ኪዳን አካል ይሆናሉ፡፡ ወይንም ደግሞ በክርስቶስ ማመናቸውን በእምነት ቃላቸው ያረጋግጣሉ፡፡ መደበኛ የአባልነት መብት ማረጋገጫ ሥርዓት የሌላቸው፣ ወይም ጥምቀትን የመሳሰሉ የቃል ኪዳን ማረጋገጫ ልምምድ የሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት፣ በመደበኛነት በሚሰጧቸው ትምህርቶች በትጋት የሚካፈሉትን የቃል ኪዳን አባልነት መብታቸውን ያስጠብቁላቸዋል፡፡ ወይም ደግሞ፣ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 7 ቁጥር 14 እንዳስተማረው፣ የሚያምኑ ወላጆች ወይም የትዳር ጓደኛ ካላቸው የዚህ መብት ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

ለምሳሌ፣ በብሉይ ኪዳን፣ የእስራኤል መንግሥት ምንም እንኳን እያንዳንዱ ሰው ለመዳን የሚያበቃ እምነት የሌለው ቢሆንም በጥቅሉ ግን የቤተክርስቲያን አካል ነበረች፡፡ ቢያንስ ቢያንስ፣ ሁሉም በመንግሥቱ ውስጥ ይኖሩ ነበር፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ እግዚአብሔር በዘፍጥረት ምዕራፍ 17 እንዳዘዘው፣ በወንዶቹ መገረዝ ምክንያት ብቻ ሁሉም የእግዚአብሔር ኪዳን በረከት አካላት ሆነዋል፡፡

በአዲስ ኪዳንም፣ ተመሳሳይ የሆነ ነገር እንመለከታለን፡፡ በቤተክርስቲያን ስብሰባዎች የሚካፈል ሰው የቤተክርስቲያን አካል ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ይህም አማኝነቱን ያወጀውን፣ የተጠመቀውን፣ የአማኝ ልጆችና የትዳር አጋሮችን አንዳንድ ጊዜም የቤት ሰራተኞቻቸውንና አገልጋዮቻቸውን

ጭምር የሚያካትት ይሆናል፡፡ ለአብነት ያህል፣ ጳውሎስ ለተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ሲጽፍ፣ ከእነዚያ አብያተ ክርስቲያናት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያለው ሰው ሁሉ እንዲያነብበው በሚል ዓላማ ነበር፡፡ ጳውሎስ ክርስቲያኖች እውነተኛ አማኞች መሆናቸውን እንዲፈትኑ ሲያሳስባቸው፣ በመካከላቸው የማያምኑም ሊኖሩ እንደሚችሉ ጳውሎስ ሙሉ በሙሉ ይገምት እንደነበር እንረዳለን፡፡ ይህንንም 2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13 ቁጥር 5፣ የመሳሰሉትን ምንባቦች ስናነብብ እናያለን፡፡ ኢየሱስም በማቴዎስ ምዕራፍ 13 ቁጥር 24 እስከ 30 ስለ ስንዴና ስለ እንክርዳዱ ምሳሌ ሲናገር ይኸው ግምት እንደነበረው እንረዳለን፡፡ ከምሳሌው እንደምንረዳው የማያምኑትን ከቤተ ክርስቲያን ማባረር አግባብነት እንደሌለውና የራሱ ጊዜ እንዳለው እንመለከታለን፡፡ በራዕይ ምዕራፍ 2 እና 3 ኢየሱስ ደግሞ ደጋግሞ እስከ ፍፃሜ እንዲፀኑ ያሳሰበበትንም ስንመለከት ይህንኑ እንገነዘባለን፡፡ ይህም ሁሉ ሆኖ አዲሱን ኪዳን ማፍረስ የሚያስከትለውን ፍርድና ማስጠንቀቂያም ዕብራውያን ምዕራፍ 6 ከቁጥር 4 እስከ 8 እና ምዕራፍ 10 ቁጥር 29 ውስጥ እንመለከታለን፡፡

አንዱን ለምሳሌ ብንወስድ፣ እስኪ በዕብራውያን ምዕራፍ 10 ቁጥር 29 የተጻፉ ቃላትን አድምጡ፡

> የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያከፋፋ፥ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል? (ዕብ 10፥29)

በዚህ ጥቅስ፣ የዕብራውያን ፀሐፊ እያመለከተ ያለው ከእግዚአብሔር ጋር የቃል ኪዳን ትስስር በማድረግ ከተቀደሱም በኋላ ኢየሱስን መካድ እንደሚቻል ነው፡፡ የተቀረው የምዕራፉ ክፍል ግልፅ እንደሚያደርገው፣ በዚህ ስፍራ የተቀመጠው ቅጣት በሲያል ለዘላለም መቃጠል ነው፡፡

> *ኢየሱስ እንደተናገረው፣ በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ "ስንዴና እንክርዳዶች" ዘወትር እንደሚኖሩ ማስታወስ ጠቃሚ ነው፡፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰዎች ይኖራሉ፤ ደግሞም የሚያስመስሉም ይኖራሉ፡፡ ልክ ለኢየሱስ የታመኑ ደቀመዛሙርት እንደነበሩ ሁሉ፣ በመካከላቸውም ይሁዳ እንደነበረው ዓይነት ማለት ነው፡፡ በጳውሎስም ደቀመዛሙርት መካከል ዴማስ ነበር፡፡ ስለዚህም፣ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እነዚህ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ [ዶ/ር ዶናልድ ዊትኒ]*

ይህ የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ቅይጥ ባህርይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚፈጠሩ አለማመኖችና ስህተቶች ንቁና የተጠበቅን ልንሆን እንደሚገባ የሚመለከት ነው፡፡ በተመሳሳይም መንገድ፣ ምንም እንኳን የማያምኑትም በአገልግሎቶቿ ውስጥ ቢሳተፉም ቅድስናዋ የተጠበቀ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ስለዚህ፣ የእግዚአብሔርን ቅዱስ ስርዓቶች የተከበሩ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ጳውሎስ በፊሊጵስዩስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 14 እስከ 18 እንዳስተማረው በግብዝነትም ሆነ እጅግ ደካማ በሆነ መንገድ

ቢሰበክም፣ የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቃል ልናከብር ይገባል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ቅድስና ቤተክርስቲያንን በእግዚአብሔር ፊንታ እንዳንመለከት ማስጠንቀቂያም ነው፣ ደግሞም ከሰው ኃጢአትና አለማመን ባሻገር እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን የሚጠቀምባት የመሆኑ ዋስትናም ነው፡፡

ስለ ምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ግንዛቤ በልቡናችን ይዘን፣ የማትታየዋን ቤተ ክርስቲያን ሃሳብ እንመልከት፡፡

# የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን

የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ማኅበረሰብ አካል የሆኑትን ሁሉ የምታካትት ብትሆንም፣ የማትታየዋ ቤተክርስቲያን ግን የምታካትተው በድነት ከክርስቶስ ጋር የተባበሩትን ብቻ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ አንዳንድ ጊዜ "እውነተኛዪቱ ቤተክርስቲያን" ተብላ ትጠራለች፡፡ የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉት መካከል የጥቂቶቹ ብቻ የሆነች አድርገን ልናስባት እንችል ይሆናል፡፡ በጥቅል አነጋገር፣ በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙና በትክክል ድኛለሁ ብለው የሚያስቡ ሰዎችን የመዳናቸውን ነገር ዘወትር እንዲያስቡ ልናሳስባቸው ይገባል፡፡ መቼም እውነታው በመዝሙር 44 ቁጥር 21 እና የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ቁጥር 8 እንደምንመለከተው ልብን ማየት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑ ነው፡፡ በውጤቱም፣ አሁን ባለንበት የታሪክ ወቅት ውስጥ የማትታየዋን ቤተክርስቲያን በእርግጠኝነት የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ የማትታየዋ ቤተክርስቲያን በአንድ ወቅት በምድር ላይ የኖረች መሆኑን አስቀድመን ማወቅ አስፈላጊ ቢሆንም፣ በተጨማሪም የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በየትኛውም ዘመን የኖረን አማኝ፣ ማለትም ከክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት በፊትና በኋላም የኖሩትን እንደምታካትት ልንገነዘብ ይገባል፡፡

አብዛኛውን ጊዜ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ከማትታየዋ ቤተክርስቲያን ይልቅ ስለ ምትታየዋ ቤተክርስቲያን ይናገራሉ ሆኖም ለተደራሲያኖቻቸው ድነትን አስመልክቶ ነገሩን በጥንቃቄ የመመርመርን ጥቅም ያመለክታሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ግን ልብ ሊባሉና ሊጠቀሱ የሚገባቸው ነገሮች መኖራቸውን ማሰብ ይገባል፡፡ ለምሳሌ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 እና በ1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 19 እና 20 ያለው ሁኔታ ይጠቀሳል፡፡ በራዕይ ምዕራፍ 2 እና 3 ከተጻፉት ደብዳቤዎች መካከል አንዳንዶቹ ስለ ተደረሲያኖቻቸው ብዙ ተስፋ የሚያደርጉ አይመስሉም፡፡ በጥቅሉ ግን፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ደራሲዎች አንባቢዎቻቸው እግዚአብሔርን እንዲያምኑና እንዲታመኑበት በታማኝነትም እንዲታዘዙት ይጠብቁባቸዋል፡፡ ግቡም የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በጠቅላላ የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አካል እንድትሆን፣ እያንዳንዱም ሰው የታመነ ሆኖ እንዲገኝ ነው፡፡

ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ፣ ቤተክርስቲያኑን ፈጽሞ ያነፃታል፡፡ የማያምኑትንም ከመካከልዋ ያስወግዳል፣ ያን ጊዜም የማትታየዋ ቤተ ክርስቲን ከምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ ዓይነት ትሆናለች፡፡ ይህንንም ማቴዎስ ምዕራፍ 7 ከቁጥር 21 እስከ 23፣ ምዕራፍ 13 ከቁጥር 24 እስከ 30፤ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 12 እስከ 15 እና 1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 4 ከቁጥር 17 እስከ 19 በመሳሰሉት ክፍሎች እንመለከተዋለን፡፡ እስከዚያን ጊዜ ድረስ ግን፣ በማትታየዋ ቤተ ክርስቲን ውስጥ የሚገኑ ሰዎች ማንነት በእርግጠኝነት የሚታወቀው በእግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

ስለዚህ በአሁን ዘመን ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎች በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ያለች የመሆኗን እውነታ መረዳት እጅግ ጠቃሚ አንድምታ እንዳለው ሊታወቅ ይገባል፡፡ የመጀመሪያውና ትልቁ እንድምታ ቤተ ክርስቲያን በመደበኛነት ወንጌልን ልትሰማ የሚያስፈልጋት መሆኑ ነው፡፡ በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማያምኑ እንዳሉ እናውቃለን፡፡ ይህም ማለት የቤተክርስቲያን አባልነት ለድነታችን ዋስትና አይሆንም ማለት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ የድነትን ወንጌል ለሌሎች ብቻ ሳይሆን ለራሳችንም ጭምር መስበካችንንና ማስተማራችንን ልንቀጥል ይገባናል ማለት ነው፡፡ በየማኅበረ ምዕመናኖቻችን የሚገኙ የማያምኑ ሰዎች ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ ስለ መጋበዛቸውና የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አባል ስለመሆናቸው እርግጠኛ ልንሆን ይገባል፡፡

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ መሆኗን ሲያረጋግጥ፣ ቤተክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር በቃል ኪዳን የተሳሰረች፣ ልክ እንደ እግዚአብሔር ልዩ ሕዝቦች የተለየች፣ ለአገልግሎት የተሰጠች ናት ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም የቤተክርስቲያን የመጨረሻ ግቧ ግብረገባዊ ንፅህና ነው ማለት ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ አሁን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ አማኞች ልምምድም በክርስቶስ ግብረገባዊ ንፅሕና ውስጥ እንዲሰወሩ ያደርጋቸዋል ማለት ነው፡፡ አልፎም፣ የእግዚአብሔርን ህግጋት ለመጠበቅ ራሳችንን ስንሰጥ፣ ከምንሠራው ኀጢአት ዘወትር እንነፃለን፣ እግዚአብሔር ለእኛ ወዳዘጋጀውም የፍፁም ቅድስና ግብ እየቀረብን እንሄዳለን ማለትም ነው፡፡

እስካሁን ድረስ ቤተክርስቲያን ጠቃሚነቷንና ሥልጣኗን ስለገኘችበት ስለ ቤተ ክርስቲያን መለኮታዊ ፈቃድ/ ስምምነት እና ቤተክርስቲያን ለእግዚአብሔር የተቀደሰች የመሆኗን ሃሳብ ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ ሦስተኛውን ርዕሳችንን ለመመልከት እንዘጋጃለን፡፡ ያም እውነታ ቤተ ክርስቲያን ካቶሊካዊት ወይንም ዓለም አቀፋዊት ናት የሚለው ነው፡፡

# 4.ካቶሊካዊት

ካቶሊክ በሚለው ቃል ላይ የምናደርገው ውይይት ሦስት ክፍሎች አሉት፡፡ አንደኛ፣ "ካቶሊክ" የሚለውን ቃል ፍቺ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ የምትታየዋን ቤተ ክርስቲያን ካቶሊካዊነት እንመለከታለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ወደ ማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ካቶሊካዊነት እንመለሳለን፡፡ አስቀድመን "ካቶሊክ" የሚለውን ቃል ፍቺ እንመልከት፡፡

## ትርጓሜ

ቀደም ባለው ትምህርት እንዳነሳነው፣ ካቶሊክ ማለት ዓለም- አቀፋዊ ማለት ነው፤ ወይንም በሁሉም ቤተ እምነቶች የሚገኙ ክርስቲያኖችን ሁሉ የሚያካትት ማለት ነው፡፡ "ካቶሊክ" የሚለው ቃል፣ catholicus የሚለው የላቲን ቃል ፍቺ ሲሆን፣ ከዚያም ደግሞ Kata ከተባለው የግሪክ መስተዋድድ እና holos ከተሰኘው ቅፅል የተወሰደ ነው፣ ፍቺውም "ምሉዕ" ወይም "ፍፁም" ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ቃል የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንን የሚያመለክት አይደለም፡፡ ይልቁኑ፣ ክርስቶስን በታማኝነት በሚከተሉ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለው አንድነት መግለጫ ነው፡፡

በዚህ ተከታታይ ትምህርት መጀመሪያ አካባቢ እንደተመለከትነው፣ ዛሬ በእጃችን ያለው የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የተወሰደው ከጥንታውያኑ የጥምቀት ሥርዓት የእምነት መግለጫዎች መሆኑን ታስታውሳላችሁ፡፡ እነዚህ ጥንታዊ የእምነት መግለጫዎች በተጻፉበት ወቅት፣ በመላው ዓለም የሚገኙ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት በአንድ፣ ሁሉን በሚያስተባብር የቤተክርስቲያን አስተዳደር ስር አልተካተቱም ነበር፡፡ ስለዚህ፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ስለ ካቶሊካዊነት ሲናገር፣ የክርስቲያን ማኅበረ- ምዕመናንን ድርጅታዊ ቅርፅ በአሳቤ ይዞ አልነበረም፡፡ ይልቁኑ፣ ከየትኛውም ደርጅታዊ ልዩነታቸው ይልቅ በሁሉም እውነተኛ ክርስቲያናዊ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ስላለው የመንፈስ አንድነት ነበር የሚናገረው፡፡ አሁን ባለንበት የታሪክ ዘመን፣ "ካቶሊክ" የሚለው ቃል ሁሉን አቀፍ ነው፡፡ ቀደም ብሎም የነበረው ፍቺ "ቤተክርስቲያን" የሚለው ስም ሁሉንም ክርስቲያናዊ ድርጅቶች እንዲወክል የታለመ ነበር፡፡

ይህ ሃሳብ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 2፣ ደብዳቤውን በእዚህ መንገድ ሲያብራራ ካስተማረው ጋር ይጣጣማል፡

> በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት፥ የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት፤ (1ኛ ቆሮ 1፥2)

በዚህ ስፍራ፣ ጳውሎስ በቆሮንቶስ የሚገኙትን የተለያዩ አብያተክርስቲያናት “በቆሮንቶስ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን” ብሎ በጥቅሉ ሲጠራቸው፣ የትም ይኑሩ የት በክርስቶስ ስም የሚጠሩትን ሁሉ የምታካትተዋ የትልቋ ቤተ ክርስቲያን አካላት እንደሆኑ ለማመልከት ነበር፡፡

በሦስተኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ፣ የቀርጤሱ ሳይፐሬይን ቤተ ክርስቲያንን ለመግለፅ የጳጳሳትን ወይንም የቀሳውስትን ድርሻ በማስቀመጡ ላይ ትኩረት ያደርግ ጀመር፡፡ በ68ኛ ደብዳቤውም ይህንን ብሎ ነበር፡

*ቤተክርስቲያን ተብለው የሚጠቀሱት ከቀሳውስት ጋር የሚተባበሩት ናቸው … ቤተ ክርስቲያን፣ እርሷም ካቶሊካዊት፣ በፍፁም የማትቆራረስና የማትከፋፈል አንድ የሆነችው ናት፣ ነገር ግን አንዳቸው ከሌላቸው ጋር በሚጣጣሙ ቀሳውስቷ አማካይነት የተያያዘች እና በአንድነት የተሳሰረች ናት፡፡*

ለሳይፐሬይን፣ የቤተክርስቲያን አንድነት የተመሠረተው በሃይማኖት መሪዎቹ ና በአገልግሎታቸው ላይ ነው፡፡ ይህ አመለካከት እያደገ ሲመጣ፣ ክርስቲያኖችም የቤተክርስቲያን አንድነት ከአስተዳደሩ አንድነት ጋር የተያያዘ መሆኑን እየተቀበሉት መጡ፡፡ ቤተ ክርስቲያን በመላው ዓለም በየትኛውም ስፍራ የምትገኝ አንድ ድርጅት ነች ምክንያቱም ጳጳሳቷና ቀሳውስቷ በመላው ዓለም ይኖራሉና፡፡

በዚህ ነጥብም ቢሆን፣ “ካቶሊክ” የሚለው ቃል ሁሉን አቀፍ፣ ማለትም በክርስቶስ ኢየሱስ ስም የሚጠሩና ለቤተክርስቲያን ትውፊታዊ አስተምህሮዎች ታማኝ የሆኑትን ሰዎችና ማኅበረ ምዕመናንን የሚያካትት ይዘት ነበረው፡፡

ሆኖም፣ ቆይቶ፣ ቤተክርስቲያን በመለያየት ተበታተነች፡፡ ለምሳሌ፣ በ1054 (እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር) የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን እውቅና ነሳች፡፡ የምስራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትም የሮማዋን ካቶሊክ ቤተክርስቲያንን እውቅና ነፈገች፡፡

በዚህ ወቅት፣ እነዚህ ቤተ ክርስቲያናት “ካቶሊክ” የሚለውን ቃል በአዲስ መንገድ ለተወሰነ ጎራ ብቻ በሚሰጥ መንፈስ መጠቀም ጀመሩ፡፡ እያንዳንዳቸውም የራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን ካቶሊክ ወይንም ዓለም አቀፋዊ ናት ማለት ጀመሩ፣ ይህንንም ሲሉ ዋጋ ያላት ቤተክርስቲያን የእነርሱ ብቻ እንደሆነች ለማመልከትና ተፎካካሪዎቻችን ናቸው የሚሏቸውን ለማውገዝ ነበር፡፡

በኋላም፣ በ16ኛው ክፍለ ዘመን የተሃድሶ እንቅስቃሴ ሲጀምር፣ አብዛኛዎቹ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናት የተለያየ አቀራረብ ይዘው ብቅ አሉ፡፡ በመሠረታዊ ደረጃ፣ ወደ መጀመሪያው የሃይማኖት መግለጫው ትርጓሜ ማለትም “ካቶሊክ” ለሚለው ቃል ወደነበረው ቀደምት ሁሉን አቀፍ ትርጓሜ ተመለሱ፡፡ ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ጋር

በማጣጣም፣ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉም ክርስቲያናዊ ቤተ ክርስቲያናት በክርስቶስ ራስነት ስር በመንፈስ አንድነት የሚኖሩ መሆኑን አረጋገጡ፡፡ ይህም አንድነት ምንም እንኳን ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት በቤተክርስቲያን አስተዳደር ዙሪያ መተባበር ቢያቅታቸውም የተጠበቀ ሊሆን እንደሚገባውና እያንዳንዱ ቤተእምነት የሚያበረክተው አዎንታዊ አስተዋፅዖ ሊናቅ እንደማይገባው እውቅና ሰጥተው ነበር፡፡

በዘመነኛው ዓለም የቤተ ክርስቲያንን ካቶሊካዊነት እውቅና መስጠት ማለት በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ የተጠቀሱትን አስተምህሮዎች አጥብቀው የያዙ አብያተ ክርስቲያናትን ዋጋ መስጠት ማለት ነው፡፡ በሁሉም የታመኑ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚገኙ ክርስቲያኖች ሁሉ በክርስቶስ የኪዳን ራስነት ስር ናቸው፣ እናም እውነተኞቹ አማኞች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች የተባረኩ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ በሁሉም ታማኝ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በሚገኙ እውነተኛ ክርስቲያኖች የጸጋ ስጦታ ለመጠቀም የምንጓጓ ልንሆን ይገባል፣ በተጨማሪም በተቻለ መጠን አንዳችን ሌላችንን ለማገልገል ፈቃደኞች ልንሆንም ይገባል፡፡

ይህንን "ካቶሊክ" የሚለውን ቃል ፍቺ በልቡናችን ይዘን፣ የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን "ካቶሊክ" ተብላ የምትጠራባቸውን መንገዶች እንመልከት፡፡

# የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን

የካቶሊካዊነትንና የምትታየዋን ቤተ ክርስቲያን መረዳታችንን ስናዋህዳቸው፣ የምትታየዋን ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን፡- በክርስቶስ ራስነት ስር ከእግዚአብሔር ጋር በቃል ኪዳን ተሳስረው የሚኖሩ ህዝቦች ዓለም አቀፋዊ ኅብረት ብለን ፍቺ ልንሰጣት እንችላለን፡፡ ይህ ኅብረት የመንፈስ አንድነት እንጂ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር አንድነት አይደለም፡፡ ሁሉንም ክርስቲያናዊ ማኅበረ ምእመናን በአንድነት የሚያስተዳድር የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ሊኖር አይችልም፡፡ ይልቁኑ፣ የምትታየዋ ቤተክርስቲያን አንድነት የሚመሠረተው እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን ከአንዱ እግዚአብሔር ጋር በሚኖራት የቃል ኪዳን ትስስርና በአንዱ ክርስቶስ ቃልኪዳናዊ ራስነት ስር በመተዳደሯ ላይ ነው፡፡

ከታሪክ እንደምንረዳው፣ የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ካቶሊካዊነቷን የምታሳየው በተለያዩ መንገዶች ነው፡፡ በአንዳንድ ልማዶች፣ በቤተክርስቲያን አስተዳደሯ ትገለጣለች፡፡ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ስታበዛ እየሰፋች ትሄዳለች፣ እያንዳንዱም አዲስ አገልጋይ ከእርሱ ቀድመው አገልጋይ በሆኑ ሰዎች እጅ ተጭኖ ተጸልዮለት ይሾማል፡፡

በጥቅሉ ግን ፕሮቴስታንቶች የቤተ ክርስቲያን አንድነት የሚያርፈው በክርስቶስ ባለን እምነትና በመንፈስ ቅድስ ሥራ እንጂ በተሾሙ አገልጋዮቿ የማያቋርጥ መተካካት ላይ አለመሆኑን አፅንኦት

ይሰጣሉ፡፡ በዚህም ምክንያት፣ የመንፈስ አንድነት ባለበት ሁሉ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የቃል ኪዳን ትስስር ያላቸው ሰዎች በክርስቶስ ስም ከተሰበሰቡ አዳዲስ ቤተ እምነቶች ሊነሱ ይችላሉ ማለት ነው፡፡ ፕሮቴስታንቶች የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ካቶሊካዊት ናት የሚለውን አጽንተው ይናገራሉ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ጋር የቃል ኪዳን ትስስር ያላቸው ሰዎች፣ በክርስቶስ ራስነትና በመንፈስ አንድነት በሁሉም ቦታ ስለሚገኙ ነው፡፡

በዛሬ ዘመን የሚገኙ በርካታ ክርስቲያኖች ከሚጋፈጡዋቸው የተለመዱ ችግሮች መካከል አንዱ፣ ካቶሊካዊቷ ወይንም ዓለም አቀፋዊቷ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አካል የሆነችው የትኛዋ ናት ብለን እንቀበል የሚለው ነው፡፡ በአብዛኛው የዓለማችን ክፍሎች፣ ክርስቲያን ነን ብለው የሚያውጁ በርካታ ዓይነቶች አሉ እነርሱም ጤነኛ ክርስትናን የሚያራምዱ ሆነው ወደ አንድ ወይንም ወደ ሁለት ፅንፍ የሚያዘነብሉ ናቸው፡፡ ክርስቲያን ነን ብለው የሚያውጁትን ሁሉ እጃቸውን በሰፊው ዘርግተው የሚቀበሉ፣ አለዚያም ደግሞ በእነርሱ ጠባብ አስተሳሰብ ቤተ እምነታችን ወይንም ማኅበረ ምዕመናችን ከሚሉት ውጪ ያለውን ሁሉ የሚያገልሉ ናቸው፡፡

ለዚህ ችግር የሚረዳ መፍትሄ የሚገኘው በሦስቱ ትውፊታዊ የቤተክርስቲያን ምልክቶች ውስጥ ነው፡፡ እነዚህ ምልክቶች የተቀናበሩት በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በስኮትላንዳዊው ጆን ኖክስ ቢሆንም በእርሱ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ፕሮቴስታንቶችን አስተሳሰብ ይወክላሉ፡፡ በመሠረታዊነትም፣ ምልክቶቹ ክርስቲያኖች እውነተኛዎቹንና አስመሳዮቹን ማኅበረ ምዕመናን እንዲለዩ ረድተዋቸዋል፡፡

> *የቤተ ክርስቲያን አድራሻ የት ነው? የሚለውን ለማወቅ የቤተክርስቲያን ምልክቶች እጅግ አስፈላጊ ናቸው፣ ምክንያቱም እንደ እውነታው፣ ማንኛውም ነገር ተነስቶ ራሱን ቤተ ክርስቲያን ብሎ ሊጠራ ይችላልና ነው፡፡ በታላቁ ነገረ-መለኮታዊ ቀውስ ወቅት፣ ማለትም በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተነሳው ተሃድሶ የተነሳው ጥያቄ፣ "እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን የምትገኘው የት ነው?" የሚል ነበር፡፡ ስለዚህም የተሃድሶ አራማጆቹ፣ በትልቅ ጥንቃቄ የቤተ ክርስቲያንን ምልክቶች እንዲህ በማለት አስቀምጠውታል፡፡ "የቤተክርስቲያን አድራሻ ማለት በመሠረቱ ከውጭ የሚሰቀለው ማስታወቂያ አይደለም፡፡ የቤተ ክርስቲያኑም ህንፃ አርክቴክቸር አይደለም፡፡ ተወደደም ተጠላም፣ ከሁሉ አስቀድሞ፣ የእግዚአብሔር ቃል የሚሰበከበት ስፍራ ነው፡፡" የእግዚአብሔር ቃል ትክክለኛ ስብከት በሚሰበከበት ስፍራ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን በዚያ አለች፡፡ የቤተ ክርስቲያን ስርዓቶችና ፕሮግራሞች በትክክለኛው መንገድ በየሚተዳደሩበት ስፍራ ሁሉ፣ በዚያ ቤተ ክርስቲያን አለች፡፡ በኋላ ደግሞ፣ በተለይ የቤተክርስቲያንን የስነ-ሥርዓት እርምጃ ያካተተው ምልክት ተጨመረ፡፡ ይህም ያለ ስነ-ሥርዓት እርምጃ የቤተ ክርስቲያን ንፅህና አጅ የሰጠ መሆኑን በመረዳት ሲሆን፣ ይህ ካልሆነ*

*በስተቀር ቤተክርስቲያን ንፅህናዋና ማንነቷ የጎደፈ ይሆናል ማለት ነው፡፡ [ዶ/ር አር. አልበርት ሞህለር]*

የምትታየዋን ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሦስት ትውፊታዊ ምልክቶች እንመልከታቸው፡፡ አስቀድመንም በእግዚአብሔር ቃል ስብከት እንጀምር፡፡

የእግዚአብሔርን ቃል የራሱ የማድረግ፣ የመተርጎም፣ የማዛመድና የማወጅ ብቸኛ ባለመብት ነኝ ሊል የሚችል ቤተ ክርስቲያን ወይንም ቤተ እምነት የለም፡፡ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እና ቤተ እምነቶች ቅዱሳት መጻሕፍትን የመተርጎምና የማስተማር መብት ያለን እኛ ብቻ ነን የሚል ድምፅ ያሰማሉ፡፡ ጥቂቶቹ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳታችን ከሌሎቹ ይልቅ እውነተኛ ይሆን ዘንድ አብርኆትን አግኝተናል ይላሉ፡፡ ግን የትኞቹንም ምልክቶች የእግዚአብሔር ቃል ስብከትን ጨምሮ ያለ እንከን የሚገልጥ ቤተ ክርስቲያን የለም፡፡ እግዚአብሔር ቃሉን የሰጠው ለምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በጠቅላላ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስንም እንረዳ ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ለሁሉም የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል፡፡ ይህንንም በ1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 15፣ ዕብራውያን ምዕራፍ 4 ከቁጥር 11 እስከ 13 እና ምዕራፍ 6 ከቁጥር 4 እስከ 6 ላይ እናገኛለን፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ በማቴዎስ ምዕራፍ 28 ቁጥር 20፣ 1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 4 ቁጥር 17፣ 2ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 15 እና ምዕራፍ 3 ከቁጥር 14 እስከ 17 እንደምንመለከተው፣ ቅዱሳት መጻሕፍት የምትታየዋን ቤተ ክርስቲያን በጠቅላላ የእግዚአብሔርን ቃል እንድታነብብ፣ እንድትረዳና እንድታስተምር ያሳስባሉ፡፡

ሁለተኛው የቤተ ክርስቲያን ምልክት የጥምቀትና የጌታ ራት ስርዓቶች ትክክለኛ አስተዳደር ነው፡፡ እነዚህ ስርዓቶች ለሁሉም የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን እንጂ፣ ለአንዱ ወይንም ለሌላኛው ቤተ ክርስቲያን ብቻ አልተሰጡም፡፡

እነዚህን ስርዓቶች እንደ እግዚአብሔር ቃል ማስተዳደር በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚገኙ እያንዳንዳቸው ምኅበረ ምዕመናን የተሰጠ እድልም ሃላፊነትም ነው፡፡ ይህንንም በማቴዎስ ምዕራፍ 28 ቁጥር 19 ላይ አጥምቁ ተብሎ በተሰጠው ታላቅ ተልዕኮ ውስጥ እና ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 13 እስከ 17 ስለ ጥምቀት ባስተማረው ውስጥ እንመለከተዋለን፡፡ በተጨማሪም፣ ኢየሱስ በሉቃስ ምዕራፍ 22 ከቁጥር 15 እስከ 20 የጌታን ራት ሲደነግግ በተናገረው ውስጥ እንመለከተዋለን፡፡ በዚያም ውስጥ የጌታ ራት ለመንግሥቱ ሁሉ እና በእርሱ የኪዳን ራስነት ስር ለሚተዳደሩ ሁሉ እንደሆነ አመልክቷል፡፡ አብዛኞቹ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የሌሎች አብያተ ክርስቲያናትንና ቤተ እምነቶችን ስርዓቶች እውቅና እንዲሰጡና እንዲቀበሉ ምክንያት የሚሆኑዋቸው እነዚህን የመሳሰሉት ምንባቦች ናቸው፡፡

ሦስተኛው የምትታየዋ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ትውፊታዊ ምልክት መደበኛው የቤተ ክርስቲያን የስነ-ሥርዓት እርምጃ፣ ለምሳሌ፣ ከአባልነት ማገድ ነው፡፡

የቤተክርስቲያንን የስነ-ሥርዓት እርምጃ፣ በተለይም መታገድን ደስ የሚሰኝበት ክርስቲያን አይኖርም፡፡ ይህም አብያተ ክርስቲያናት መደበኛውን የስነ-ሥርዓት እርምጃ መጠቀምን ደግመው ደጋግመው እንዲተዉት አድርጓቸዋል፡፡ እርግጥ ነው ነገሩን እስከ ጊዜው መተውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማስጠንቀቂያ ምልክትነትም አለው፡፡ የዚህንም ፍንጭ በማቴዎስ ምዕራፍ 13 ከቁጥር 24 እስከ 30 ስለ ስንዴውና ስለ እንክርዳዱ በተነገረው ምሳሌ ውስጥ እናገኘዋለን፡፡

የስነ-ሥርዓት እርምጃው በትክክል እየተወሰደም እንኳን፣ የሰውየውን ኃጢአት በስነ-ሥርዓት እርምጃ ብቻ ለመገላገል አዳጋች የሚሆንበት ወቅት አለ፡፡ ይህም ጉዳዩ ቤተክርስቲያንን አደጋ ውስጥ የሚጥልና ስሟን የሚያጎድፍ ሲሆን ነው፡፡ ይህን በመሰለው ወቅት፣ የስነ-ሥርዓት እርምጃው ቤተክርስቲያንን ከመከላከልና ሰውየውንም ወደ ንስሓ ከመምራት አኳያ ሊከናወን ይገባዋል፡፡ መደበኛውን የስነ-ስርዓት እርምጃ አስመልክቶ የማናገኛቸው ቅዱሳት መጻሕፍታዊ መሠረቶች በማቴዎስ ምዕራፍ 16 ቁጥር 19፣ ምዕራፍ 18 ቁጥር 18፤ ዮሐንስ ምዕራፍ 20 ቁጥር 23 እና ቲቶ ምዕራፍ 3 ቁጥር 10 ላይ እናገኛለን፡፡ በተግባር የተፈፀመበትንም 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ከቁር 1 እስከ 13 በመሳሰሉት ክፍሎች እንመለከታለን፡፡ የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በጠቅላላ የክርስቶስ ስለሆነችና ክርስቶስን በምድር የምትወክል ስለሆነ፣ በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በየትኛውም ስፍራ የሚገኙ ሁሉ አግባብነት ያለውን የቤተ ክርስቲያን የስነ-ሥርዓት እርምጃ ተግባራዊ በማድረግ የክርስቶስን ህዝብ ሊከላከሉና የእርሱንም ክብር ሊጠብቁ ይገባል፡፡

ዛሬም ቢሆን እኛ የቤተክርስቲያንን ምልክቶች ዋጋ ልንሰጣቸው አስፈላጊ ነው፡፡ ማኅበረ ምዕመናችን በምትታየዋ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ክልል ውስጥ፣ በክርስቶስ ራስነት ከእግዚአብሔር ጋር በቃል ኪዳን ተሳስረው የሚኖሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ይጠቅሙናል፡፡ በተጨማሪም አስመሳዮችንና የቤተ ክርስቲያንን ጠላቶች ለይተን እንድናውቃቸው፣ ክርስቲያኖችም ከእነዚህ መሳይ ቡድኖች እንዲጠበቁ ለማስጠንቀቅና እነዚህም ቡድኖች ጌታችንንና የእርሱን ወንጌል እንደማይወክሉ ለተቀረው ዓለም ማወጅ እንድንችል ያደርጉናል፡፡ በአገልግሎት በምንሰማራበትም ወቅት የቤተ እምነቶቻችን ድንበር ሳይከልለን አብረን እንድንሠራም ያበረታቱናል፡፡ የክርስቶስ አካል በእኛ ቤተ ክርስቲያንና ቤተ እምነት ብቻ የማትወሰን፣ ትክክለኛው የክርስቶስ ወንጌል በሚሰበክበት ሁሉ ያለች መሆኗን ከተገነዘብን፣ በዚያች በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ሁሉ ለመቀበል እንበረታታለን፡፡

እስካሁን ድረስ የምትታየዋን ቤተ ክርስቲያን ዓለማቀፋዊ ተፈጥሮ ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያንም ካቶሊካዊት ወይንም ዓለም አቀፋዊ የምትሆንባቸውን ጥቂት መንገዶች እንመልከት፡፡

# የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን

ስለ ማትታየዋ ቤተክርስቲያን ያለንን መረዳት ስለ ካቶሊካዊነት ካለን መረዳት ጋር ስናዋህደው፣ የማትታየዋን ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን፡ በዘመናት ሁሉ ለመዳን ከክርስቶስ ጋር የተባበሩ ህዝቦች፡፡ ብለን ፍቺ ልንሰጣት እንችላለን፡፡ ቀደም ብለን እንደተናገርነው፣ የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን የምትታየዋ አካል ስለሆነች፣ በማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ ሰው ሁሉ በክርስቶስ ራስነት ስር ከእግዚአብሔር ጋር የቃል ኪዳን ትስስር ያለው ህዝብ ነው፡፡ ሆኖም የማትታየዋን ቤተ ክርስቲያን ለመለየት፣ ፍቺያችን የሚያተኩረው ከምትታየው ቤተ ክርስቲያን ጋር እንዴት እንደምትለያይ ይሆናል፡፡

ስለ ማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ካቶሊካዊነት የምናሰላስልባቸው በርካታ መንገዶች ቢኖሩም፣ በሁለቱ ላይ ብቻ እናተኩራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ሊያድን የሚችል አንድ ብቻ ስለሆነ የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፋዊ ናት፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ወደ አዳኙ ሊመራን የሚችል አንድ ሃይማኖት ብቻ ስለሆነ የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፋዊ ናት፡፡ አስቀድመን አንድ አዳኝ ብቻ የመኖሩን ሃሳብ እንመልከት፡፡

# አንድ አዳኝ

ለሰው ዘር ሁሉ የተሰጠ አዳኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት በግልፅ ያስተምራሉ፡፡ ሊያድነን የሚችል ኃይል ያለው፣ ደግሞም ሊያድነንም የፈቀደ እርሱ ብቻ ነው፡፡ ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 4 ቁጥር 12 እንደጠቀሰው፡

> መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና። (ሐሥ 4፥12)

ለሰው ዘር ሁሉ የዘላለም አዳኝ ሆኖ የተሰጠ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ቁጥር 6 እነዚህን ቃላት ሲናገር ጌታ ራሱ ይህንን እውነት አውጇል፡፡

> ኢየሱስም፡- እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። (ዮሐ 14፥6)

*ሊያድነን የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ለምን ሆነ? መቼም አዳኙ ፍፁም ሰው ፍፁምም አምላክ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ስለዚህም ኢየሱስ በእኛ ምትክ ይሆን ዘንድ፣ ስለ እኛ ይሰዋ ዘንድ፣ ፍፁም ሰው ሊሆን ተገብቶታል፡፡ ያንንም ሃላፊነት የሚወጣ ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡*

*በመሠረቱም ይህ ነገር የተዘጋጀው፣ ገና ከጥንት እግዚአብሔር ከዳዊት ዘር የሆነውን አንበሳ ይልቅ ዘንድ ሲሾመው ማለትም ዳዊት የእግዚአብሔር መሲህ እንዲሆን የተቀባውም እንዲሆን ይህም በቤዝዎት ታሪክ ውስጥ እንዲከናወን ሲፈቅድ ነው፡፡ እናም ኢየሱስ ከዳዊት ዘር የሆነው ታላቅ ንጉሥ ነው፣ ይህንንም ቢሮ የያዘው ኢየሱስ ነው፣ እንግዲያው ብሉይ ኪዳን በጠቅላላ እኛን ሲያዘጋጀን የነበረው ለኢየሱስ መምጣት ነበር፡፡ ስለዚህ፣ ህዝቡን ሁሉ ከኃጢአት የማዳኑን መስፈርት ያሟላ ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡ [ዶ/ር ጆን ፍሬም]*

ኢየሱስ የፕሪስቢቴሪያኑ፣ የባፕቲስቱ፣ የአንግሊካኑ፣ የሜቶዲስቱ፣ የሉትራኑ፣ የሮማ ካቶሊኩ፣ የምስራቅ ኦርቶዶክሱ እና በየትኛውም በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ቤተ እምነቶች ሁሉ ብቸኛ አዳኝ ነው፡፡

የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አንድ ብቻ ናት ምክንያቱም የዳኑት ሁሉ የሚተባበሩት ከአንዱ ክርስቶስ ከአንዱ አዳኝ ጋር ብቻ ነውና፡፡ የአንድነታችን ምንጭ እርሱ ብቻ ነው፡፡ እርሱ ሊከፋፈል ስለማይችል፣ እኛም አንለያይም፡፡

የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ካቶሊካዊት ወይንም ዓለም አቀፋዊት የመሆኗ ሁለተኛው ሃሳብ ወደ ክርስቶስ የሚመራን አንድ ሃይማኖት ብቻ ያለ ከመሆኑ እውነታ ጋር የሚዛመድ ነው፡፡

# አንድ ሃይማኖት

ከሁሉ አስቀድሞ ክርስትና መዳንን የማግኛ ዘዴ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ የቃል ኪዳን ትስስር መሆኑን መገንዘብ ጠቃሚ ነው፡፡ ስለዚህ፣ እንደሌሎቹ ሃይማኖቶች ሁሉ፣ ክርስትና በመሠረታዊነት ድነትን የማግኛ ዘዴ ሳይሆን ከእግዚአብሔርና ከህዝቡ ጋር የሚደረግ ወዳጅነት መሆኑን መናገር ያስፈልጋል፡፡ አዎን፣ እምነት ከእግዚአብሔር ጋር በትክክለኛው ኅብረት የምንቀመጥበት መንገድ ነው፡፡ ትልቁ ጥያቄ ግን፡ በእግዚአብሔር ፊት ስትቆም መታወቂያህ ምንድን ነው? በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ታማኝ ዜጋ ነህን? እግዚአብሔር ሲያይህ፣ በክርስቶስ የደም ኪዳን የተሰወረን አንድ ሰው ያያልን? ወይስ የእርሱ ጠላት መንግሥት ዜጋ ነህ? በራስህ ጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም የምትጥር ነህን፣ ይህ ከሆነ ስለ በደልህ ዋጋ የሚከፍል ማን ሊሆን ነው?

የሚያሳዝነው፣ በተሳሳቱ ሃይማኖቶች ውስጥ ያሉ ሰዎች የጠላት መንግሥት አባላት ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ህዝብ ወገን አይደሉም፣ እናም ስለዚህ፣ የክርስቶስ አይደሉም ሊሆኑም አይችሉም፡፡ ወደ አዳኛችን መቅረብ የምንችልበትን ዕድል የሚሰጠን ክርስትና ብቻ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ክርስትና ሰዎች በሌሎች ሃይማኖቶች፣ ምንም እንኳን ሰዎቹና

ሃይማኖቶቹ መልካም መሻት ያላቸው ቢመስሉም ሊድኑ ይችላሉ የሚለውን አማራጭ ውድቅ የሚያደርገው ለዚህ ነው፡፡

*እንደምናውቀው፣ ክርስቲያናዊ ያልሆኑ በርካታ ሃይማኖቶች አሉ፣ አንዳንድ ጊዜም "የዓለም ታላላቅ ሃይማኖቶች" ተብለው ይጠራሉ፡፡ የዚህም ምክንያቱ ትልቅነታቸውና ተፅዕኖአቸው ነው፡፡ ስለዚህም ክርስቲያን ያልሆነ አንድ ሰው፣ በዓለም ላይ በሚገኙት ታላላቅ ሃይማኖቶች በአንዱ በታማኝነት ከተሳተፈ፣ የዚያንም ሃይማኖት አስተምህሮና ልምምዶች በትጋት የሚከፈል ከሆነ፣ ልምምዶቹንም ከልቡ የሚያደርግ ከሆነ፣ ክርስቶስን ባያውቅም እንኳን ወደ መንግሥተ ሰማያት አይገባምን? ምናልባትም ስለ ክርስቶስ ባይሰማስ? መጽሐፍ ቅዱስ ግን በዚህ ረገድ ግልፅ ነው፡፡ በዮሐንስ 14፥6 ኢየሱስ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ በግልፅ ይመለከተዋል፡፡ ስለራሱም "እኔ መንገድ፣ እውነት ሕይወትም ነኝ" እነዚያም በበቂ ሁኔታ ግልፅ ካልሆኑ "በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" በማለት ይናገራል፡፡ [ዶ/ር ዶናልድ ዊትኒ]*

*ሰዎች በየትኛውም ሃይማኖት ውስጥ ቢኖሩም ከእግዚአብሔር የወል ጸጋ የተነሳ አንዳንድ መልካም ነገሮች በሕይወታቸው ይገለጣሉ፡፡ ግን በአንፃሩ በሰዎች ሕይወት ውስጥ እጅግ የከፉ ነገሮችንም እንመለከታለን፡፡ እናም የእግዚአብሔርን ቅድስናና የሰው ዘርን ውድቀት ስንገነዘብ፣ ወደ እግዚአብሔር መምጣትና ከእርሱም ጋር ህብረት ማድረግ ከባዶ ስነ-ምግባራዊ ጨዋነት የዘለለ ነገር እንደሚያሻ እንገነዘባለን፡፡ በዚህ ኃጢአተኛ ማንነታችን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ነገር ማከናወን አንችልም፡፡ ስለዚህም የሚያስፈልገን ቤዛና አዳኝ አንጂ ባዶ ሃይማኖታዊ ልምምድ አይደለም፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ወዳለን ግንኙነት ሊመልሰን የሚችል ብቸኛ መንገድ ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡ [ዶ/ር ኤሪክ ኬ. ቶኔስ]*

እንደተናገርነው፣ የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመደበኛነት የሚገኙት ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ በርካታ የነገረ-መለኮት ምሁራን ከምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውጪ ለሚገኙ ሰዎች በመደበኛነት ድነት ሊገኝ አይችልም ብለው ነጥቡን ግልጥ ያደርጉታል፡፡ ያም ማለት፣ አንድ ሰው የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አካል ካልሆነ የመዳን መደበኛ እድል አይኖረውም፡፡

ከ200 እስከ 258 ዓ.ም. የኖረው፣ የቀደምት ቤተ ክርስቲያን አባት የሆነው ሳይፕሪያን፣ On the Unity of the Church በተሰኘው ጽሑፉ እንዲህ አስቀምጦታል፡

*ከቤተ ክርስቲያን የተለየና ራሱን ለምንዝርና አሳልፎ የሰጠ፣ ከቤተ ክርስቲያን ተስፋዎችም አብሮ ተለይቷል፤ የክርስቶስንም ቤተ ክርስቲያን ያቃለለም የክርስቶስን ብድራት*

*አይቀበልም፤ እርሱ እንግዳ፣ የረከሰ እና ጠላት ነው፡፡ ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር አባቱ፣ ቤተ ክርስቲያንም እናቱ ልትሆን አትችልም፡፡*

በዚህ ስፍራ፣ ሳይፕሪን የምትታየዋን ቤተ ክርስቲያን ትተው የሄዱትን እየተሟገተ ነው፡፡ ነጥቡም የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አካል እስካልሆኑ ድረስ የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አካል ሊሆኑና የክርስቶስን ብድራት ሊቀበሉ እንደማይችሉ ማሳሰብ ነው፡፡ ይህ ሙግት የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር በቃል ኪዳን የተሳሰረች ስለ መሆኗ ከተነጋገርነው ጋር የሚስማማ ነው፡፡

የጉዳዩ እውነታም ድነት ራሱ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን በረከት ነው የሚለው ነው፡፡ ይህንንም በኤርምያስ ምዕራፍ 31 ከቁጥር 31 እስከ 34፣ ሉቃስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 69 እስከ 75፣ ሮሜ ምዕራፍ 11 ቁጥር 27፣ ዕብራውያን ምዕራፍ 7 ከቁጥር 22 እስከ 25 እና በበርካታ ሌሎች ቦታዎችም እንመለከተዋለን፡፡ አንዱን ለምሳሌ ለማንሳት፣ ኢየሱስ በሉቃስ ምእራፍ 22 ቁጥር 20 ላይ የጌታን ራት ሲደነግግ የተናገረውን አድምጡ፡

> እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ፡- ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው። (ሉቃስ 22፥20)

ጌታ ታልፎ በተሰጠባት ምሽት፣ ስለ በደላችን ስርየት የሚፈሰው ደሙ አዲስ ኪዳን እንደሚሆን ተናግሯል፡፡ በሌላ አነጋገር፣ በክርስቶስ ደም የሆነው ድነት የሚገኘው በእርሱ ኪዳን ብቻ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ኪዳን ከምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ጋር እስከሆነ ድረስ፣ ድነትም በመደበኛነት የሚገኘው በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በኩል ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ሰዎች በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወደ እምነት ሲመጡ፣ ወይንም የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በወንጌል አገልግሎት ሰዎች እንዲለወጡ ስታደርግ ነው፡፡ እርግጥ ነው፣ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ጋር ምንም ግንኙነት በሌለው መንገድ ሊድኑ ይችላሉ፡፡ ይህ ሲሆን ግን፣ አንድ እንግዳ ነገር ወይንም ያልተለመደ ነገር እንደተከናወነ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፋዊ ስለሆነች፣ ለእግዚአብሔር ኪዳን ታማኝ የሆኑት ብቻ ይድናሉ፡፡ በሌሎች ሃይማኖቶች ውስጥ የሚገኙ ሰዎች የሃይማኖታቸውን ስርዓት ጥንቅቅ አድርገው በመፈፀምና በዚያም መልካም በመሆን ብቻ ወደ መንግሥተ ሰማያት የመግባት ተስፋ የላቸውም፡፡ ወንጌልን ልንሰብክ ይገባናል፡፡ ለሰዎችም ስለ ብቸኛው አዳኝ ልንነግራቸው ይገባል፡፡ በምድር ላይ ወደምትገኘው የእግዚአብሔር መንግሥት፣ ወደ ቃልኪዳኑ ማኅበረሰብ ልናመጣቸው፣ የመንግሥቱንም ጌታና ንጉሥ እንዲወድዱና እንዲታዘዙ ልናስተምራቸው ይገባል፡፡ ለእኛ ለዳንነው የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ካቶሊካዊነት ትልቅ ብርታትን ይሰጠናል፡፡ ምክንያቱም

ለእኛ በክርስቶስ አንድ የመሆናችን መግለጫ ነውና፡፡ ወደ ክርስቶስ ላልመጡት ግን እጅግ አስፈሪ ማስጠንቀቂያ ነው፡፡

ስለ ቤተ ክርስቲያን በተማርነው ትምህርት፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን መለኮታዊ ፈቃድ/ስምምነት፣ ደግሞም ቤተክርስቲያን ቅዱስ እና ካቶሊካዊት ወይንም ዓለም አቀፋዊ ስለ መሆኗ ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ፣ ወደ መጨረሻው ዐቢይ ርዕሳችን፡ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳን አንድነት ስለ መሆኗ ሃሳብ ለመነጋገር እንዘጋጃለን፡፡

# 5. የቅዱሳን አንድነት/ኅብረት

"ቅዱስ" በሚለው ቃል ላይ ባደረግነው ውይይት፣ ቅዱሳን የሚለው አባባል ጠቅለል ባለ መንገድ በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኘውን እያንዳንዱን ሰው ሲያመለክት፣ ለየት ባለ መንገድ ደግሞ በማትተታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኘውን እያንዳንዱን ሰው ያመለክታል፡፡ ስለዚህ፣ ስለ ቅዱሳን አንድነት ስንነጋገር፣ እስካሁን ባልተመለከትነው አባባል፣ አንድነት ወይንም ኅብረት በተሰኘው ላይ ትኩረት እናደርጋለን፡፡

ጥንታዊው የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ግሪክኛ ቅጂ፣ ኅብረት ለሚለው ቃል Koinonia (κοινωνία) የሚለውን ተጠቅሟል፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ይህንን ቃል በመደበኛነት የሚጠቀሙት በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል ያለውን ኅብረት በተለይም ከእግዚአብሔር ጋር ካላቸው አንድነት አንፃር ያለውን ለማመልከት ነው፡፡ ይህንንም የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ቁጥር 42፣ 2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13 ቁጥር 14 እና 1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 3 ላይ እናገኘዋለን፡፡

አዲስ ኪዳንም Koinonia (κοινωνία) የሚለውን ቃል ያለን ከማካፈል ጋር - በተደጋጋሚም ቁሳቁስንና ገንዘብን ከማካፈል ጋር በማያዝ ይጠቀምበታል፡፡ ይህንንም በሮሜ ምዕራፍ 15 ቁጥር 16፣ 2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 9 ቁጥር 13 እና ዕብራውያን ምዕራፍ 13 ቁጥር 16 ላይ እንመለከተዋለን፡፡ በተጨማሪም ወንጌልንም ከማካፈል አንፃር አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ በፊልጵስዩስ ምዕራፍ 1 ቁር 5 እና ፊሊሞና 6 ላይ እንደተገለፀው በጅማ ስብከት ሳይሆን በአንድ ለአንድ ቅርርቦሽ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረገውን ማለት ነው፡፡

ከነዚህ ሃሳቦች ጋር አብሮ በሚሄድ መንገድ፣ "ኅብረት" የሚለው ቃል በተለምዶ የሚዛመደው በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል ያለውን ኅብረት ከማመልከት ጋር ነው፤ የጋራ የሆኑ ነገሮቻችንን መካፈልን፤ ከእኛ ጋር በሚከፋፈሉትም ሰዎች መካከል በእርስ በርስ መግባባት ላይ የተመሠረተ የመደጋገፍ እንድምታም በውስጡ አለ፡፡

የቅዱሳንን አንድነት ስንዳስስ፣ ውይይታችንንም አሁን በውል እየተለመደ ባለው መለያው ዙሪያ እንዲያጠነጥን እናደርጋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን የሚገኘውን ኅብረት እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ በማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ያለውን ኅብረት እንመለከታለን፡፡ በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በሚኖረው ኅብረት እንጀምር፡፡

# የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን

በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው ኅብረት በርካታ ገፅታዎች ቢኖሩትም፣ እኛ ግን በሦስቱ ላይ ብቻ እናተኩራለን፡ በመጀመሪያ፣ ጸጋን የማግኛ መንገድ፤ ሁለተኛ፣ የጸጋ ስጦታዎች፤ ሦስተኛ፣ ንብረት/ቁሳቁስ፡፡ ጸጋን የማግኛ መንገድን በመመልከት እንጀምር፡፡

# ጸጋን የማግኛ መንገድ

ጸጋን የማግኛ መንገዶች እግዚአብሔር ለሕዝቡ ጸጋን ለመስጠት በመደበኛነት የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ወይንም መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ከሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን መሥራቾች መካከል አንዱ ጆን ዌስሊ፣ የጸጋን መንገድ የአብዛኛዎቹን ክርስቲያኖች ትውፊታዊ አመለካከት በሚያንፀባርቅ መልክ ገልጦታል፡፡ እስኪ በሚልክያስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 7 ላይ ተመሥርቶ በጻፈው 16ኛ መልእክቱ ላይ የጻፈውን አድምጡ፡፡

> *ስለ “ጸጋን የመቀበያ መንገዶች” የምረዳው እግዚአብሔር ወደዚህ ፍፃሜ ለማምጣት አስቀድሞ ያዘጋጃቸውን ውጫዊ ምልክቶችን፣ ቃሎችን ወይንም ተግባራትን ነው፡፡ ማለትም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያዘጋጀውን የሚከላከልበትን፣ የሚያጸድቅበትን ወይንም የሚቀድስበትን ጸጋ የሚያስተላልፍባቸው መንገዶች ናቸው፡፡ [ጆን ዌስሊ]*

> *የጸጋን መንገድ፣ አንዳንዶች በየመጣንበት ትውፊት ላይ ተመሥርተው ከተለያዩ ሃይማኖታዊ ወጎችና መንፈሳዊ ስነ-ሥርዓቶች ጋር ሊያዛምዱት ሲሞክሩ ስሰማ፣ “እንዴት ሊሠሩ ይችላሉ?” ብዬ እጠይቃለሁ፡፡ በምላሹ ግን ዘወትር ማለት የምፈልገው፣ “ጨርሶ አይሠሩም፡፡ የሚሠራው እግዚአብሔር ነው፤ የሚሠራው የእግዚብሔር ጸጋ ነው” የሚለውን ነው፡፡ የጸጋ መንገድ ግን፣ ያንን ጸጋ የምንቀበልበትን ሂደት ወይንም ዕድል ያዘጋጅልናል፡፡ በእኛ ሕይወት ውስጥ በሥራ ላይ ባለው ጸጋ ላይ ትኩረት እናደርግ ዘንድ ወቅትና ጊዜ ይቀጥሩልናል፡፡ ስለነዚህ ነገሮች ሳስብ ስለ ቧንቧነታቸው ማሰብን እወዳለሁ፡፡ ውሃውን ከቧንቧው ልናምታታው አይገባም፡፡ ልንቀበለው የምንሻው የሕወትን ውሃ ነው፡፡ ይህንን የሕይወት ውሃ ወደ እኛ የሚያፈስሱልን ግን ቧንቧዎቹ ናቸው፡፡ ከእነርሱም የተነሳ*

*ይሕይወትን ውሃ እንጠጣለን፣ የጸጋ መንገዶች የሕይወትን ውሃ እንድንጠጣ ያስችሉናል፡፡ [ዶ/ር ስቲቭ ሃርፐር]*

ከተግባራዊነት አንፃር ስንናገረው፣ እግዚአብሔር ጸጋን በሕይወታችን እንዲሠራ የሚያደርግባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፣ እነርሱም ተቀናቃኞቻችን፣ መከራዎቻችን፣ እምነት፣ በጎ አድራጎት እና ኅብረት ራሱ ናቸው፡፡ በተለምዶ ግን የነገረ-መለኮት ምሁራኑ፣ በተለይ በሦስቱ የተለዩ የጸጋ መንገዶች ላይ ያተኩራሉ፡ የእግዚአብሔር ቃል፣ የጥምቀትና የጌታ ራት ሥርዓቶች እና ጸሎት ናቸው፡፡ የእነዚህ የሦስቱም የጸጋ መንገዶች  ባለቤት የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ስትሆን፣ ያመኑትንማ የማያምኑትንም ያካትታል፡፡

ትውፊታዊውን የፕሮቴስታንት ክርስቲያናዊ አስተምህሮ አጠቃልሎ ያቀረበው፣ የዌስት ሚኒስቴሩ አጭር ካቴኪዝም፣ በጥያቄና መልስ ቁጥር 88 ላይ የጸጋን መንገድ በዚህ መንገድ ገልጦታል፡

ጥ፡ ክርስቶስ የቤዛነቱን በረከቶች ወደ እኛ ያመጣባቸው ውጫዊ መንገዶች ምንድን ናቸው?

መ፡ ክርስቶስ የቤዛነቱን በረከቶች ወደ እኛ ያስተላለፈባቸው ውጫዊ መንገዶች፡ የተቀደሱ ድንጋጌዎቹ፣ በተለይም ቃሉ፣ ሥርዓቶቹና ጸሎት ናቸው፡፡ ሁሉም ሊድኑ በተመረጡት ሕይወት ውስጥ በጎ ተፅዕኖን የሚያሳድሩ ናቸው፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት ስለነዚህ የጸጋ መንገድ ትሩፋቶች በሮሜ ምዕራፍ 10 ቁጥር 14፣ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 10 ቁጥር 17 እና 1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 12 እና 21 ላይ  ይናገራሉ፡፡

ምንም እንኳን የመቤዠት በረከቶች ለዳኑት ብቻ፣ ያም ለማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ቢሆንም፣ ሥርዓቶቹ ግን ለምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በጠቅላላ ነው፡፡ የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ልክ እንደ ስሟ የማትታይ መሆኗን አስታውሱ፡፡ ማን በውስጥዋ እንዳለ አናውቅም፡፡ የራሷ የሆነ የአምልኮ ሥርዓት የላትም፡፡ የራሷ የሆነ አገልግሎት የላትም፡፡ የራሷ የሆነ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የላትም፡፡ እነዚህ ነገሮች ሁሉ የተደነገጉት ለምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ በተመሳሳይም መንገድ፣ ጸጋን የመቀበያ መንገዶቻችን ሁሉ ማለትም ስብከታችን፣ ጥምቀታችን፣ የጌታ ራት ሥርዓታችን እና ጸሎቶቻችን ሁሉ በሌሎችም የሚደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሁሉም የሚታዩ ናቸው፡፡ የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን የምትጋራቸው ነገሮች ናቸው፣ ስለዚህም የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት አካላት ናቸው፡፡

ጸጋን የመቀበያ መንገዶች እግዚአብሔር በመደበኛነት የመቤዠትን በረከቶች በሕይወታችን ተግባራዊ የሚያደርግባቸው እጅግ አስፈላጊ የሆኑ የዘወትር ድንጋጌዎች ናቸው፣ ስለዚህ በሙላት ልንጠቀምባቸው ይገባል፡፡ የሚለውጠውን ወንጌል ልንሰብክ፣ ጥበብንና ብስለትን የሚያስገኝልንን የእግዚአብሔርንም ቃል ልናስተምር ይገባናል፡፡ ወንጌልን በጉልህ የሚወክሉና እኛንም

ከእግዚአብሔር ኪዳን ጋር የሚያስተሳስሩንን ሥርዓቶች ልንጠብቃቸው ይገባል፡፡ ከእግዚአብሔርም ጸጋንና ምሕረትን እንድንቀበል፣ ለለውጥና ለብስለት፣ ኀጢአትንም የምንቋቋምበትን ረድኤት እንድናገኝ፣ ከክፉውም እንዲጠብቀንና በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድንቀበል ልንጸልይ ይገባናል፡፡ በእነዚህና በሌሎችም በርካታ መንገዶች፣ ጸጋን የመቀበያ መንገዶች ዋጋ የሚሰጣቸው የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ናቸው፡፡

ጸጋን ከመቀበያ መንገዶችም ባሻገር፣ የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን የወል የሆኑ የጸጋ ስጦታዎችም አሏት፡፡

# የጸጋ ስጦታዎች

የጸጋ ስጦታዎች ለምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በጠቅላላ የተሰጡ ናቸው ስንል፣ በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን የሚገኝ ሰው ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነው ማለታችን አይደለም፡፡ ፈጽሞ አይደለም፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሚሆኑት ያመኑት ብቻ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን፣ መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ስጦታዎችን የምትታየዋን ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት ዓላማ ቢጠቀምባቸውም ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት ለአንዳንዶቹ፣ በቅድስናቸው እንዲያድጉ ለማገዝ እና እየበሰሉ እንዲሄዱ ለማድረግ የሚያስችላቸው ነው፡፡ ለሌሎቹ ደግሞ፣ አስቀድሞ ወደ እምነት የሚያመጣቸው ነው ማለት ነው፡፡ በሁሉም ምክንያቶች ግን፣ በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኝ የትኛውም ሰው ከመንፈሳዊ ስጦታዎች ጋር ግንኙነት ያለው ሲሆን፣ በተወሰነ መጠንም በእነርሱ ውስጥ የመሳተፍ ዕድልም አለው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ መንፈሳዊ ስጦታዎች በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በጠቅላላ ሁሉ የሚገለገልባቸው ናቸው ማለት ትክክል ነው ማለት ነው፡፡

የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በጠቅላላ የምትካፈላቸው መንፈሳዊ ስጦታዎች በተለያየ መንገድ ይገለጣሉ፡፡ በመጀመሪያ፣ በመደበኛ የአምልኮ አገልግሎታችን ውስጥ እንገለገልባቸዋለን፡፡ ይህንንም በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 14 ከቁር 13 እስከ 26 በግልፅ እናየዋለን፡፡ ሁለተኛ፣ ስጦታዎቹ የተሰጡት አካሏን በጠቅላላ ለማነፅ ነው፡፡ ይህንንም በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 ከቁጥር 4 እስከ 7 እና ኤፌሶንምዕራፍ 4 ከቁጥር 3 እስከ 13 ላይ እንመለከተዋለን፡፡ ሦስተኛ፣ በተለይም ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 14 ከቁር 21 እስከ 22 ላይ ልሳን ለማያምኑት ምልክት እንደሆነ ተናግሯል፡፡ አራተኛ፣ በዕብራውያን ምዕራፍ 6 ከቁር 4 እስከ 6 እንደተጻፈው፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ግን የማያምኑ የጸጋ ስጦታዎችን ለመጠቀም አሻፈረኝ በማለታቸው ይፈረድባቸዋል፡፡ በእነዚህም መንገዶች፣ ያመኑትም ሆነ ያላመኑት ለቤተ ክርስቲያን ከተሰጠው የጸጋ ስጦታ እንደሚካፈሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ግልፅ ያደርጉልናል፡፡

ልክ እንደ ጸጋ መቀበያ መንገዶች ሁሉ፣ የጸጋ ስጦታዎችም ለምትታየዋ የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ጠቀሜታቸው የጎላ ነው፡፡ እውነትን ለማወጅና የጠፉትን ለመመለስ ይጠቅሙናል፡፡ አማኞችንም

በእምነትና በብስለት ለማሳደግ ይጠቅሙናል፡፡ ምህረት፣ እንግዳ መቀበልና የመሳሰሉት በርካታ ስጦታዎችም የእግዚአብሔርን ህዝብ ምድራዊ መሻት ለማሟላት እጅግ ይጠቅሙናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለህዝቡ ስጦታዎችን ሰጥቶ በምናይበት ጊዜ ሁሉ፣ እነዚያን ስጦታዎች ለሁሉ ጥቅም እንዲገለገሉባቸው እና በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን የሚገኝ የትኛውም ሰው እንዳይከለከል ልናበረታታቸው ይገባል፡፡

ኅብረት በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉም ያሏቸውን ንብረቶችና ቁሳቁሶች በጋራ በመከፋፈልም ይገለጣል፡፡

# ንብረት/ቁሳቁስ

ኅብረት ወይንም *koinonia* (κοινωνία) ለሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስና በቀደምት ቤተ ክርስቲያን ከተሰጡት ፍቺዎች መካከል፣ በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ያሉ ሰዎች ካላቸው ሃብትና ንብረት ለተቸገሩ ያካፍሉ የነበረበት ሁኔታ አንዱ ነው፡፡ *koinonia* (κοινωνία) የሚለው ቃል በሮሜ ምዕራፍ 15 ቁር 26፣ 2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 8 ቁጥር 4፣ ምዕራፍ 9 ቁጥር 13 እና ዕብራውያን ምዕራፍ 13 ቁር 16 ላይ ተደጋግሞ የተጠቀሰው ለችግረኞች ከማዋጣት ጋር ነው፡፡

ምንም እንኳን *koinonia* (κοινωνία) የሚለው ቃል በአገልግሎት ላይ ባይውልም፣ የኅብረት ፅንሰ ሃሳብ በቀደሙት ክርስቲያኖች ልምምድ ውስጥ ይታይ ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ቁጥር 44 እና 45፣ በምዕራፍ 4 ቁር 34 እና 35 እንደምንመለከተው፣ በርካታ ቀደምት ክርስቲያኖች ያላቸውን ሁሉ ሸጠው ገንዘቡን ለቤተ ክርስቲያን ያመጡ ነበር፡፡ በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ ጀግኖች ክርስቲያኖች ሌሎችን ነጻ ለማውጣትና ድኖችን ለመመገብ የሚያስችል ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ራሳቸውን ለባርነት ይሸጡ ነበር፡፡

ከ30 እስከ 100 ዓ.ም. ድረስ የኖረውና ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባት የነበረው ክሌመንት፣ በተለምዶ 1ኛ ክሌመንት ተብሎ በሚታወቀውና ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ደብዳቤው ስለዚህ ልምምድ ጽፏል፡፡ ከዚያ ደብዳቤ ምዕራፍ 55 ላይ እነዚህን እስኪ አድምጡ፡

> *በእኛ መካከል ለሌሎች መስዋዕት ይሆኑ ዘንድ ራሳቸውን ለባርነት አሳልፈው የሰጡ በርካቶች አሉ፡፡ ሌሎችም በርካቶች ደግሞ፣ራሳቸውን ለባርነት በመሸጥ ያገኙትን ገንዘብ ለሌሎች ምግብን ለመግዛት አውለውታል፡፡ [ክሌመንት]*

በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኅብረት የሚለው ቃል እጅግ ብርቱ ነበር፣ አማኞችም ሌሎችን ከራሳቸው እጅግ አስበልጠው ይመለከቱ ነበር፣ ሃብታቸውንም ብቻ ሳይሆን ነፃነታቸውንም እንኳን ስለ ሌሎች አሳልፈው ይሰጡ ነበር፡፡

በ2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 3 እስከ 5 ጳውሎስ የጻፈው ቃል አስተሳሰባቸውን ለማብራራት ይጠቅማል፡፡ በዚያ ስፍራ የጻፈውን እስኪ እናድምጥ፡

> እንደ ዓቅማቸው መጠን ከዓቅማቸውም የሚያልፍ እንኳ ወደው እንደ ሰጡ እመሰክርላቸዋለሁና።
> ለቅዱሳን በሆነው አገልግሎት እንዲተባበሩ ይህን ቸርነት በብዙ ልመና ከእኛ ይለምኑ ነበር፥
> አስቀድመውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለጌታ ለእኛም ሰጡ እንጂ እንዳሰብነን አይደለም። (2ቆሮ 8፥3-5)

በዚህ ምንባብ፣ ጳውሎስ የመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናትን ደግነት ይገልጣል፡፡ ለምትታየዋ የጌታ ቤተ ክርስቲያን መስዋዕትነት የሞላበት ስጦታ እንዲሰጡ ያስቻላቸው አስቀድመው ለጌታ ራሳቸውን መስጠታቸው እንደሆነ ያብራራል፡፡

ካለን ሃብትና ንብረት ለተቸገሩ ማካፈል የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን እጅግ አስፈላጊ ክፍል ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን በጠቅላላ የእግዚአብሔር ህዝብ፣ የቃል ኪዳኑም ማኅበረሰብ ናት፡፡ እርሱ በውስጥዋ ስላለው ስለ እያንዳንዱ ግድ ይለዋል፣ እኛም ያን እንድናደርግ ይጠራናል፡፡ በግልጽ ለማስቀመጥም የእኛ የሆነው ሁሉ የጌታ ነው፡፡ እኛ የእርሱ ንብረት ባለ አደራዎች ብቻ ነን፡፡ ያም ማለት፣ የእኛ የበጎ አድራጎት ሥራና ስጦታችን ሁሉ ጌታ ለህዝቡ የሚሰጠው አገልግሎት አካል፣ ለዓለምም የወንጌሉ ምስክር ነው፡፡ ስለዚህም፣ ለእርሱ ታማኝ መሆን የምንፈልግ ከሆነ፣ የጌታን ንብረት ከሚያስፈልጋቸው የእርሱ ህዝቦች ልንነፍግ አይገባም፡፡

በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚገኘው የቅዱሳን አንድነት ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ በማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገለጠውን ኅብረት እንመለከታለን፡፡

# የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን

በማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገለጠው የቅዱሳን አንድነት ጋር የተያያዙ ሁለት ዋና ሃሳቦችን ተመልክተናል፡፡ በመጀመሪያ፣ ሁሉም አማኞች ከክርስቶስ ጋር ስለሚካፈሉት አንድነት እንነጋገራለን፡፡ ሁለተኛ፣ በማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ከሚገኙ ሌሎች አማኞች ጋር ስለ ምንካፈለው አንድነት እንነጋገራለን፡፡ አስቀድመን ከክርስቶስ ጋር ስላለን ኅብረት እንነጋገር፡፡

# ከክርስቶስ ጋር ያለን አንድነት

አማኞች ከክርስቶስ ጋር አንድ ስለ መሆናቸው አዲስ ኪዳን ደጋግሞ ይናገራል፡፡ ይህም ሃሳብ አማኞች በተለምዶ “በክርስቶስ” ወይንም “በኢየሱስ” ወይንም “በእርሱ” እየተባሉ በተለምዶ የሚጠቀሱበትን ያመለክታል፡፡ በአንድ በኩል፣ ይህ አንድነት ማለት ኢየሱስ በሞቱና በትንሣኤው አማኞችን ወክሎ በአብ ፊት ይቆማል ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን፣ አማኞች ከክርስቶስ ጋር ወሳኝ በሆነ መንገድ ምሥጢራዊ በሆነ መንገድ አንድ ሆነዋል ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ በአማኞች ውስጥ ይኖራል አማኞችም በእርሱ ውስጥ ይኖራሉ፡፡

> *እኔ እንደማስበው በሐዋርያው ጳውሎስ ትምህርቶች ውስጥ ማዕከላዊ ሆኖ ተለይቶ የተገለፀው እኛ ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆናችን፤ ያም እኛ የእርሱ መሆናችን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጦችን በጠቅላላ ስንመለከት፣ እኔ እንደማስበው መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን እኛ ሁላችን በአዳም አሊያም በክርስቶስ ውስጥ ነን ብሎ ነው፡፡ እርግጥ አዳም የመጀመሪያው የሰው ዘር ነው፡፡ የሰው ዘር ሁሉ የአዳም ወንድና ሴት ልጆች ሆነው ይወለዳሉ፡፡ ወደ ዓለምም በኃጢአት ይመጣሉ፡፡ ኃጢአታዊ ተፈጥሮ አላቸው፡፡ ከእግዚአብሔርም ተለይተዋል፡፡ መዳን፣ መቤዠት እና በክርስቶስ መታመን ማለትም፣ ከክርስቶስ ጋር መተባበርና የክርስቶስ መሆን ማለት ነው፡፡ ከክርስቶስም ጋር መተባበር ማለት የእርሱ ስብዕና ተካፋይ መሆን ማለት ነው፡፡ [ዶ/ር ቶም ሽሬይነር]*

> *የክርስቶስን በረከቶች ሁሉ የምንካፈለው ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆናችን ነው፡፡ ከታሪክም እንደምንረዳው እነዚህም በረከቶች፡ ጽድቅ፣ ቅድስና እና ልጅነት ናቸው፡፡ እነርሱም በድነታችን ወቅት የተቀበልናቸው ብለን የምንገልጣቸው ናቸው፡፡ ልንቀበላቸው የምንችለው በክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ እንግዲያው፣ እነዚህን በረከቶች ለመቀበል፣ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን ለእኛ እጅግ ወሳኝ እጅግም አስፈላጊ ነው፡፡ ታዲያ እነዚህን በረከቶች የምንቀበለው እንዴት ነው? ወይንም ከክርስቶስስ ጋር አንድ የምንሆነው እንዴት ነው? የምንተባበረው በእምነት ነው፣ በእምነት ብቻ፡፡ ከክርስቶስ ጋር አንድ የሚያደርገን እምነት ነው፣ ያም የእምነት ስጦታ ከእግዚአብሔር ብቻ ይገኛል፡፡ [ዶ/ር ጄፍሬይ ጄ]*

የነገረ-መለኮት ምሁራኑ በኢየሱስና በአማኞች መካከል ስላለ ስለዚህ ወሳኝ አንድነት ደግመው ደጋግመው ሲናገሩ ምሥጢራዊ ይሉታል ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደሚሠራ በግልፐ ማብራሪያ አይሰጥም ይላሉ፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ግን ይህ አንድነት አካላችንንና መንፈሳችንን እንደሚያካትት በግልፅ አስቀምጠውታል፡፡ ይህንንም ዮሐንስ ምዕራፍ 15 ከቁጥር 4 እስከ 7፣ ሮሜ ምዕራፍ 8 ከቁጥር እስከ 11 እና በሌሎችም በርካታ ስፍራዎች እናገኘዋለን፡፡

አንዱን ለምሳሌ ብንወስድ፣ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 15 የተናገረውን እስኪ አድምጡ፡

> *ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደ ሆነ አታውቁምን? …*
> *ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን አንድ መንፈስ ነው።* (1ቆሮ 6፥15-17)

ከ1834 እስከ 1892 የኖረው ታዋቂው የባፕቲስት ሰባኪ ቻርለስ ስፐርጀን፣ ከክርስቶስ ጋር ስላለን አንድነት *The Matchless Mystery* በተሰኘውና በኤፌሶን ምዕራፍ 5 ቁጥር 30 ላይ በተመሠረተው መልዕክቱ ተናግሯል፡፡ እስኪ ንግግሩን አድምጡ፡

> *በእኛና በክርስቶስ መካከል አንድ መተባበር ሆኗል … ያም አንድነት ብቻ አይደለም፤ ማንነት እንጂ፡፡ እንዲያው ከእርሱ ጋር መጣመርም አይደለም፤ የእርሱ አካል መሆን፣ የክርስቶስ ወሳኝ ምሉዕ ማንነት አካል መሆን ነው፡፡ ለእርሱ ወሳኝ የሆኑት የእርሱም ህዝብ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ [ቻርለስ ስፐርጀን]*

ከክርስቶስ ጋር ያለን አንድነት እጅግ ወሳኝ መሆኑን እንዲያውም ለክርስቶስ ለራሱ እኛ ከእርሱ ከተነጠልን ኪሳራ መሆኑን ማሰብ አስገራሚ ነው፡፡ እርሱ ስለሚወድደን ሞተልን እኛም የእርሱ ብድራቱ ፣ ርስቱም ነን፡፡ ከእርሱ ጋር በመተባበራችን ምክንያት፣ እያንዳንዱ አማኝ በመዳኑ ትልቅ ዋስትና ሊሰማው ይገባል፣ ይቅር የመባል ዋስትናም ሊሰማው ይገባል፣ በእግዚአብሔርም ፊት የመቆም ትልቅ ድፍረት ሊኖረው ይገባል፡፡ በክርስቶስ ከተገኘውና በመንፈሱም ተጠብቆ ከሚኖረው፣ ከዚህ አንድነት ብርታትን ልናገኝ ይገባናል፡፡ በክርስቶስ ከመሰወራችን የተነሳ፣ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ዐይን ፊት ፍፁማን ነን፣ ከእግዚአብሔርም ጋር በሚኖረን ኅብረት ድፍረት ሊሰማን ይገባል፡፡

ይህ ማለት ግን በኃጢአታችን አይቀጡንም ማለት አይደለም፡፡ ግን ቅጣታቸው፣ ከፍቅር የመነጨ፣ ከእግዚአብሔርም ጋር ለዘላለም በአንድነት ወደምንኖርበት ብስለትና ፍፅምና እኛን ማድረስን ዓላማ ያደረገ ነው ማለታችን ነው፡፡

አማኞች ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን አንድነት ከተመለከትን፣ በክርስቶስ ውስጥ ካሉት ሌሎች አማኞች ጋር ስለሚኖረን አንድነት እንመለከታለን፡፡

# ከአማኞች ጋር ያለን አንድነት

በማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ ሰው ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆኑ ምክንያት፣ አማኞችም በእርሱ እርስ በርሳቸው አንድ ሆነዋል፡፡ ይህንንም በሮሜ ምዕራፍ 12 ቁጥር 5፣ በገላትያ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 26 እስከ 28 ፣ በኤፌሶን ምዕራፍ 4 ቁጥር 25 እና በሌሎችም በርካታ ሌሎች ቦታዎች እንመለከታለን፡፡ በዮሐንስ ምዕራፍ 17 ቁጥር 22 እና 23 ላይ ኢየሱስ ስለዚህ አንድነት ለአብ የተናገረውን እስኪ አድምጡ፡

> እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፥ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ፥ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደ ላክኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ያውቃል። (ዮሐ 17፥22-23)

ከምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለን አንድነት ዝምድናዊና ልምምዳዊ ሲሆን፣ ከማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለን ግንኙነት ግን መንፈሳዊና መለኮታዊ ነው፡፡ ማንነታችን ከክርስቶስና ከመንፈሱ ጋር አንድ ይሆናል፡፡ በውጤቱም፣ ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 14 እስከ 16፣ በገላትያ ምዕራፍ 3 ቁር 28 እና በቆላስያስ ምዕራፍ 3 ቁር 11 እንዳስተማረው በክርስቶስ እኩል ክብርን እንቀዳጃለን፡፡ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 ቁጥር 26 እንደምናነብበው አንዳችን የሌላችን ደስታም ሆነ ህማም ተካፋዮች እንሆናለን፡፡

የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አንድነት በምድር በምትኖረዋ ቤተ ክርስቲያን የተወሰነ አይደለም፤ በመንግሥተ ሰማያት በምትኖረውም ይዘልቃል፣ ያም ማለት በሞቱትና ከጌታ ጋር ለመሆን በሄዱትም አማኞች ውስጥ ይዘልቃል ማለት ነው፡፡ ልክ በምድር የሚኖሩ አማኞች በክርስቶስ ውስጥና በክርስቶስ በኩል እርስ በርስ አንድ እንደሆንን ሁሉ፣ ከክርስቶስ ጋር አንድ ከሆኑት ማለትም አሁን በመንግሥተ ሰማያት ያሉትንም ጨምሮ ኅብረት አለን ማለት ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ይህንን ሃሳብ እንደ ዕብራውያን ምዕራፍ 11 ቁር 4 እና ምዕራፍ 12 ከቁር 22 እስከ 24 በመሳሰሉት ክፍሎች ያስተምራሉ፡፡

ቅዱሳት ይህንን እውነታ ለማስተማር ከሚጠቀሙበት አንድ አስገራሚ ምስል መካከል አንዱ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ክርስቶስ ሙሽሪት የገለጡበት ነው፡፡ ይህም የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን እንደ ክርስቶስ ሙሽሪት እንድትታይ የሚያደርጋት ነው፡፡ ይህ ግን ሊታይ የሚገባው ሙሽሪት በማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ወደ ፍፁምነት ከምትደርስበት አተያይ አንፃር ነው፡፡ ይህንንም በብሉይ ኪዳን በኢሳይያስ ምዕራፍ 54 ከቁጥር 5 እስከ 8፣ ሆሴዕ ምዕራፍ 2 ቁጥር 19 እና 20 እና

ኤፌሶን ምዕራፍ 5 ቁጥር 26 እና 27 ላይ እንመለከታለን፡፡ የዚህ ምስል ምልዐትም የሚታየው በራዕይ ምዕራፍ 19 በተገለጠችው ንፅሕት የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው፡፡

በራዕይ ምዕራፍ 19 ከቁጥር 6 እስከ 8 ዮሐንስ ያየውን ራዕይ ሲነበብ አድምጡ፡

> እንደ ብዙ ሕዝብም ድምፅ፥ እንደ ብዙ ውኃዎችም ድምፅ፥ እንደ ብርቱም ነጐድጓድ ድምፅ ያለ ድምፅ ሰማሁ እንዲህ ሲል፡- ሃሌ ሉያ፤ ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላካችን ነግሦአልና።
> የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ ሚስቱም ራስዋን ስላዘጋጀች ደስ ይበለን ሐሤትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ።
> ያጌጠና የተጣራ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ እንድትጎናጸፍ ተሰጥቶአታል። ቀጭኑ የተልባ እግር የቅዱሳን ጽድቅ ሥራ ነውና።
> (ራእይ 19፥6-8)

በዚህ ስፍራ የክርስቶስ ሙሽሪት በየዘመናቱ የተዋጁትንና እርስ በርሳቸውም ኅብረት የሚደርጉትን ቅዱሳን ሁሉ በውስጥዋ ይዛለች፡፡ ሁላችን የቅዱሳን የጽድቅ ሥራ የሆነውን አንድ ዓይነት የሰርግ ልብስ ለብሰን በአንድነት እንቆማለን፡፡

አማኞች እርስ በርሳቸው በክርስቶስ አንድ ናቸው ከሚለው እውነታ ውስጥ ቅዱሳት መጻሕፍት በርካታ የተዛምዶ ነጥቦችን ያወጣሉ፡፡ እያንዳንዱ አማኝ ለክርስቶስ ዋጋ ያለውና በጣም አስፈላጊ መሆኑን ያስተምራሉ፡፡ እርስ በርስ እንድንከባበር፣ አንዳችንም ሌላችንን እንድናገለግል ያስተምሩናል፡፡ አንዳችን ለሌላችን ሩኅሩሆች፣ መልካሞች፣ ጨዋዎች፣ ታጋሾችና ይቅር ባዮች እንድንሆን ያስተምሩናል፡፡ ሌሎች ሰዎች ለእኛ እንዲያደርጉልን በምንፈልገው መንገድ ለሌሎች እንድናደርግ፣ እንዲያውም ራሳችን ለራሳችን ልናደርግ የምንፈልገውን ለሌሎች እንድናደርግ ያስተምሩናል፡፡ እኛ ከክርስቶስ ጋር ካለን ኅብረት የተነሳ፣ ልክ የእኛ የሰውነታችን ክፍሎች ለእኛ እንደሆኑልን ሁሉ እነርሱም ለእኛ እንዲሁ ነው፡፡

# 6.ማጠቃለያ

በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ላይ በተማርነው ትምህርት ውስጥ፣ ትምህርተ ቤተ ክርስቲያንን ዳሰስናል፡፡ ቤተ ክርስቲያንን እንደ እግዚአብሔር ልዩ ማኅበረሰብ መለኮታዊ ፍቃዷንና ስምምነቷን ተመልክተናል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ የመሆኗን እውነታ፣ ማለትም የተለዩና ንፁህ መሆናቸውን ተወያይተንበታል፡፡ ካቶሊካዊነቷንና ዓለም አቀፋዊነቷንም ተነጋግረንበታል፡፡ የቅዱሳን ኅብረት የምትሆንባቸውን መንገዶችም አብራርተናል፡፡

እንደ ዘመናዊ ክርስቲያኖች፣ የቤተ ክርስቲያን ልምምዳችን በመጽሐፍ ቅዱሱ ዘመን ወይንም የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ በተቀረፀበት ዘመን ከነበረችው እጅግ ልዩ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሰመርባቸው የሚገቡ የሕይወት እውነታዎች ግን መቼም ቢሆን አይለወጡም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ዛሬም የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ህዝብ ናት፡፡ ወንጌልን ለዓለም ሁሉ የምታደርስ እና መንግሥቱንም በዓለም የምትመሠርት አገልጋዩ ናት፡፡ እኛ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ለጌታ የተቀደስን ነን፡፡ እኛ መንግሥቱ ነን፡፡ እኛ ሕዝቡ በእርሱም ኅብረት ያለን ነን፡፡ ጌታ ራሱም በእኛ አልፎ ይሠራል፡፡